# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 207 መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## «በአገሪቱ የተሻለ ሰላም ማምጣት የመንግሥት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው»

- ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ



ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- አገራችን ላይ የተሻለ ሰላም እና ለውጥ ለማምጣት መንግሥት ብቻ ሳይሆን ሁላችንም የድርሻችንን መወጣት ይኖርብናል ሲሉ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ ገለጹ፡፡

ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሰላም አማራጭ ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በፓርላማ ላይ የገለጹት ሃሳብ ትናንትም ሆነ ዛሬ ለዚህች አገር ቀጣይነት ብቸኛው አማራጭ ሰላም መሆኑን አጽንኦት የሰጠ ነው፡፡ ስለዚህ አሁን የሚበጀው ወደ ሰላም፣ ወደ እርቅ እና ወደ ድርድር መምጣቱ ነው፡፡

በአገሪቱ የተሻለ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ምክር ቤቱ በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ የአንድ የምክር ቤት አባልን ያለመከሰስ መብት አነሳ

• የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ሹመትን መርምሮ አፅድቋል

መዓዛ ማሞ



አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው ስብሰባ የምክር ቤት አባል የሆኑት ዶክተር ጫላ ዋታ በሙስና ወንጀል በመጠርጠራቸው ያለመከሰስ መብታቸውን አንስቷል። ምክር ቤቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሹመትንም መርምሮ አጽቋል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 2ኛዓመት የሥራ ዘመን 13ኛ መደበኛ ስብሰባው የዶክተር ጫላ ዋታን ያለመከሰስ መብት አንስቷል፡፡

ምክር ቤቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ከድርቅ በኋላ የሚከሰቱ የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከል ቅድመ ጥንቃቄ እየተደረገ ነው

ገጽ 4

## የኢፕድ የሥልጠና ማዕከል ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሁለተኛ ዙር ሥልጠና መስጠት ጀመረ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠና ማዕከል ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች ሁለተኛ ዙር ሥልጠና መስጠት ጀምሯል። የመጀመሪያውን ዙር ሥልጠና የወሰዱ የአገልግሎቱ የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች በሥራቸው ላይ አወንታዊ ለውጥ እንዳመጡም አገልግሎቱ አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ በሁለተኛ

የኢፕድ የሥልጠና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ዳኜ አበራ













# ከ17 ሺ በላይ ዜጎችን ከጎዳና ላይ የማንሳት ሥራ ተሠርቷል

**ማህሌት ብዙነህ እና ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ውሎ እና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ከ17 ሺ በላይ ዜጎችን ከጎዳና ላይ የማንሳት እና የማቋቋም ሥራ እንደተሠራ የከተማው ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ ጎዳናዎች ላይ ውሎና አዳራቸውን ያደረጉ ዜጎችን ከማንሳትና ከማቋቋም ጋር ተያይዞ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን በማስመልከት በትናንትናው ዕለት መግለጫ ሰጥቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ተወካይ እና የማህበራዊ ጉዳይ ኃላፊ ወ/ሮ ገነት ቅጣው እንደገለጹት፤ በበጀት አመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ በከተማዋ ውስጥ ውሎ እና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ 17 ሺ 7 መቶ 41 ዜጎች በመንግሥት በጀት ከጎዳና ተነስተዋል፡፡

ከጎዳና ከተነሱት የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ 5 ሺ244 ዜጎች በዋነኝነት ሕፃናት እና እናቶችን ወደ ቤተሰቦቻቸው እና አካባቢያቸው የመመለስ ሥራ የተሠራ ሲሆን አምራች የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ 1 ሺ 177 ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል።

ወ/ሮ ገነት በተጨማሪም ለ400 ሕፃናት የትምህርት ዕድል እንዲያገኙና ከ100 በላይ አረጋውያንና አምሮ ህሙማን ጊዜያዊ መጠለያ ከማስገባት ባለፈ ዘላቂ የሆነ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል። ከዓለም ባንክ በተደረገ ድጋፍ 66 ሺ 548 ዜጎችን የቤት ለቤት ድጋፍና ክትትል በማድረግ ጎዳና እንዳይወጡ እየተሠራ ነው ብለዋል።



ቢሮው ከኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ ባካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው በከተማዋ ከሚገኙ 60 ሺ ውሎ እና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎች ውስጥ 97 በመቶ የሚሆኑት ከተለያዩ የአገሪቷ ክፍል የመጡ ናቸው። ከነዚህም አካባቢዎች ደቡብ ክልል፣ አማራ ክልል፣ ኦሮሚያ ክልል፣ እና ሲዳማ ክልል ከፍተኛ የፍልሰት መጠን የሚታይባቸው አካባቢዎች እንደሆኑ ጠቅሰዋል።

የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የማህበራዊ ሴፍቲኔት ኑሮ ማሻሻያ ዳይሬክተር አቶ ቢኒያም ግርማ እንደገለጹት፤ ውሎ እና አዳራቸውን ጎዳና ላያ ላደረጉ ዜጎች የሥነ-ልቦና፣ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ድጋፍ በመስጠት ወደአካባቢያቸው በፍቃደኝነት የመመለስ ሥራ እና ለ777 የሚሆኑት በቡና ለቀማ፣ 400 በኮንስትራክሽን ውስጥ እንዲሁም 113 መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ውስጥ የሥራ ዕድል የመፍጠር ሥራ ተሠርቷል።

አቶ ቢኒያም ወደ መዲናዋ የሚደረግ ከፍተኛ ፍልሰትን ለመከላከል ከሚኒስትር መስሪያ ቤቶች እና ከክልል ከተሞች ጋር በጋራ እየተሠራ ነው። በቀጣይም በመዲናዋ ውስጥ ከሚገኙ 6136 ዜጎችን በማንሳት እና በመመለስ እንዲሁም በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት እና ሥራ ፕሮጀክት ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ከ2011 ዓ.ም እስከ 2014 መጨረሻ ድረስ 27 ሺ 552 ዜጎችን ወደማገገሚያ ማዕከላት በማስገባት ወደማህበረሰብ የማቀላቀል እንዲሁም በተለያዩ የሥራ አማራጮች እንዲሳተፉ የማድረግ ሥራዎች ተሠርተዋል። 13 ሺ 765 ዜጎችን ከዓለም ባንክና ከ26 የእርዳታ ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን በከተማ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም የተቋም አገልግሎት አግኝተው ማህበረሰብ እንዲቀላቀሉ እና በሥራ እንዲሠማሩ ማድረግ እንደተቻለ አስታውሰዋል።

# በሚቀጥሉት ቀናት የሚጠበቀው ዝናብ ለእርሻ ሥራ አመቺ መሆኑ ተገለጸ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥሉት አምሥት ቀናት የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ለወቅቱ የእርሻ ሥራ አመቺ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡ ሆኖም በተወሰኑ የውኃ ዳርቻ ባሉ ማሳዎች ላይ የውኃ መተኛትና የአፈር መታጠብን ሊያስከትል ስለሚችል ከወዲሁ ጥንቃቄ መደረግ አለበት ብሏል፡፡

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በሚቀጥሉት አምሥት ቀናት የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የእርሻ ሥራ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ነው፡፡ በተለይ በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የአገሪቱ ክፍሎች የሚጠበቀው እርጥበታማ ሁኔታ በደጋማ አካባቢ ለሚዘሩ ሰብሎችም ሆነ አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት የግጦሽና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ጠቀሜታ ይኖረዋል ብሏል፡፡

በሌላ መልኩ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በሰሜን ምሥራቅ፣ በምሥራቅ፣ በመካከለኛውና በደቡብ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል በትንበያው ተጠቅሷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በመሆኑም እርጥበት እንዲበዛና ማሳዎች ላይ ውኃ እንዲተኛ ሊያደርግ ስለሚችል ተገቢው ትኩረት ተደርጎ የበዛውን ውኃ በቀላሉ ለማጠንፈፍና ለማስወገድ የሚያስችሉ ዘዴዎች ከወዲሁ እንዲተገበሩ አሳስቧል፡፡

በተመሳሳይ በውኃው ዘርፍ ሊያስከትለው የሚችል ተፅእኖ ሊኖር እንደሚችል ያሳወቀው የኢንስቲትዩቱ መግለጫ፤ በዚህ መሠረት ዝናቡ በአብዛኛው የአገሪቱ ተፋሰሶች እየጠነከረ እንደሚሄድ በመጠቆም፤ በኦሞ ጊቤ ስምጥ ሸለቆ፣ ዓባይ፣ አዋሽ፣ የታችኛውና መካከለኛው ተከዜ እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው አፋር ደናክል እና ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ሊከሰት የሚችል ቅፅበታዊ ጎርፍ እና የወንዞች ሙላት ሊያስከትለው የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስና ለማስቀረት ከወዲሁ ዝግጅቶች እንዲደረግ መክሯል፡፡

በአንፃሩ ውኃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በመጪው ወር የሚገኘውን ዝናብ ለዘላቂ የውኃ ፍጆታ ለማዋል የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ውኃ የማሰባሰብ እንዲሁም በተገቢው ሁኔታ በማጠራቀም በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባ በአፅንኦት አሳስቧል፡፡

በአጠቃላይ በቀጣይ ወር የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት በብዙ የአገሪቱ ስፍራዎች ላይ እየጠነከረ የሚሄድበት ወር እንደሆነ በመጠቆም፤ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊከሰት እንደሚችል አሳስበዋል፡፡

በዚህም መሠረት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ ኢሉአባቡራና ሰሜን ሸዋ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረሪ፣ አዲስ አበባ እና በአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም ከቀላል እስከ ከባድ ዝናብ ይኖራል፡፡

በተጨማሪም ትግራይ ክልል መካከለኛው፣ ምሥራቅና ደቡብ ትግራይ እንዲሁም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልልና ሶማሌ ክልል ዞኖች ከቀላል እስከ ከባድ ዝናብ እንደሚኖር በመጥቀስ ይህን ተከትሎ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊኖር እንደሚችል ትንበያው ጠቁሟል፡፡

# የሌማት ትሩፋት የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን በማሳደግ ረገድ ወሳኝ ሚና እየተወጣ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የሌማት ትሩፋት ፕሮጀክት የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን በማሳደግ ረገድ ወሳኝ ሚና እየተወጣ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ገለጸ፡፡

ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ የብልፅግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትና የፓርቲው የሴቶች ሊግ ሥራ አስፈፃሚዎች ትናንት በአዲስ አበባ ከተማ የተሠሩ የሌማት ትሩፋት ሥራዎችን ጎብኝተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ የሺ ወልዴ በወቅቱ እንደገለጹት፤ በሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴዎች ከኢኮኖሚው ብልጽግና ጎን ለጎን የሴቶችን የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥራ ተከናውኗል።

በአዲስ አበባ ከተማ በ11 ክፍለ ከተሞች ሴቶች ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ተላቀው ገቢያቸው እንዲያድግ ለማስቻል በተጀመሩ የሌማት ትሩፋት ሥራዎች የምግብ ፍጆታቸውን ከመቻል አልፈው ለገበያ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ተፈጥሯል ብለዋል፡፡

ከሌማት ትሩፋቱ በፊት «ምግቤን ከጓሮዬ ጤናዬ ከምግቤ» በሚል ተጀምሮ የነበረ የግብርና ሥራ ተግባራዊ ተደርጎ እንደነበር ያስታወሱት ፕሬዚዳንቷ፤ አሁን የሌማት ትሩፋቱ ከተጀመረ ወዲህ በጓሮ አትክልት፣ በወተት ላሞች፣ በግና ፍየል ማደለብ፣ ንብ በማነብና፣ በዶሮ እርባታ የተሰማሩ ሴቶች ቤተሰባቸውንና አገራቸውን በመጥቀም ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ፕሬዚዳንቷ እንዳስታወቁት፤ ሴት ልጅ ከኢኮኖሚ ጥገኝነቷ ስትወጣ ብቁና ተሰሚ ትሆናለች። የሴቶችን የልማት ተጠቃሚነት በማረጋገጥ አቅም የሚያጎለብቱና በራስ መተማመናቸውን የሚያጠናክሩ ሥራዎችን ማስፋፋት ይገባል።



የአዲስ አበባ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ በተለይ የኢኮኖሚ ውስንነት ያለባቸው ሴቶች የተሻለ ገቢ እንዲኖራቸው የሚያስችል ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። በመዲናዋ በሌማት ትሩፋት የተሳተፉ እንስቶች ውጤታማ ሥራ ማከናወናቸው በተግባር ታይቷል ብለዋል።

በመስክ ምልከታው የልምድ ልውውጥ ለማድረግና በሌማት ትሩፋቱ በትኩረት ሠርተው ውጤታማ የሆኑ ሴቶችን የሚያበረታታ ክንውን ተደርጓል ሲሉ አስረድተዋል።

ሴቶች በስፋት የሚሳተፉባቸውን የሌማት ትሩፋት ሥራዎች የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የግብዓት ችግሮችን መፍታት፣ የተሟላ የሙያ ድጋፍ ማቅረብና የገበያ ትስስር መፍጠር እንደሚገባ ወይዘሮ የሺ ገልጸዋል።

በብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ጠይባ ሐሰን በበኩላቸው፤ በመዲናዋ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየተከናወኑ ባሉ ሥራዎች ሴቶችን ከድህነት ኑሮ ማውጣት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

የፓርቲው ብልፅግና ጽሕፈት ቤት ሴቶች በሌማት ትሩፋት በስፋት እንዲሳተፉ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የኢኮኖሚ ድጋፍና የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ሴቶችን እያበረታታ ይገኛል ብለዋል።

ሴቶች ገቢያቸውን ሲያሳድጉና የኢኮኖሚ አቅማቸውን ሲያጠናክሩ የከተማዋ ሁለንተናዊ ዕድገት ለማፋጠን ያግዛል። በቀጣይም የሌማት ትሩፋት ሥራዎች ሴቶች በበለጠ እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ቂርቆስ፣ ለሚኩራና በየካ ክፍለ ከተሞች ሴቶች ያከናወኗቸው የሌማት ትሩፋት ሥራዎች ላይ የመስክ ምልከታ ተደርጓል።




ፎቶ፡- ሑዳ ኸብርሃ

# ተቋማቱ «ዲጂታል የዳኝነት አገልግሎትን» ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት ተፈራረሙ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮምና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ‹‹ዲጂታል የዳኝነት አገልግሎትን›› ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አገልግሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ ለማገዝ፣ ለዜጎች ይበልጥ ተደራሽና ፈጣን ፍትህ ለመስጠት የሚያስችል ‹‹በዲጂታል የታገዘ የዳኝነት አገልግሎትን›› ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት በትናንትናው ዕለት በኢትዮ ቴሌኮምና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መካከል ተፈርሟል፡፡

በስምምነቱ ወቅት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት እንደገለጹት፤ ስምምነቱ የዳኝነት አገልግሎቱን የሚያፋጥን ነው:: በሰው ላይ የተመሠረተውን የዳኝነት አገልግሎት ጫና በመቀነስና አገልግሎቱን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ እንዲደርስ ያደርጋል:: እንዲሁም የፍርድ ቤቶችን ሥራ ለማዘመን አንድ እርምጃ ወደፊት የሚወስድ ነው፡፡

ከፍትሕ፣ ከዳኝነት ተደራሽነትና ከእርካታ ጋር በተገናኘ ከደንበኞች ቅሬታዎች መኖራቸውን ያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህን ችግር ለመፍታት ከሚወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ አንዱ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ የተደገፉ ማድረግ ነው ሲሉ ገልጸዋል::

የአገልግሎት እርካታ ክፍተቶችን ለመሙላት እየተሠራ መሆኑን በመግለጽም፤ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የተደረገው ስምምነት ከተወሰዱ እርምጃዎች መካከል አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል:: የሚሰጠውን አገልግሎት በብዙ እርምጃ ወደፊት ያራምደዋል ሲሉም አክለዋል::

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ ቴክኖሎጂው በየቦታው የተከፈቱ ፍርድቤቶች ወይም ምድብ ችሎቶችን እርስ በርስ እንዲተሳሰሩና በመካከላቸው የሚኖረውን የመረጃ ልውውጥ እንዲቃለል ያስችላል:: የመረጃ ልውውጥን በማፋጠን በቀላሉ ለደንበኞች ተደራሽ እንዲሆን ያስችላል::

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፍሬህይወት ታምሩ በበኩላቸው፤ በስምምነቱ መሠረት ኢትዮ ቴሌኮም የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶችን ገንብቶ እንደሚያስረክብ ጠቁመዋል:: አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት፣ የመጠባበቂያ ኔትወርክና የኔትወርክ ደህንነት ያለው ዘመናዊ የሞጁላር መረጃ ማዕከል ገንብቶ እንደሚያስረክብ ጠቅሰው፤ በተጨማሪም የኔትዎርክ ኦፕሬሽን መቆጣጠሪያ ማዕከል፣ የዋይድ ኤሪያና ሎካል ኤሪያ ኔትወርክ ግንባታ እንዲሁም የሶፍትዌር ደረጃ ዋይድ ኤሪያ ኔትወርክ ማስተዳደሪያ በመገንባት እንደሚያስረክብ አብራርተዋል::

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተግባራዊ በሚያደርገው የኢ-ኮርት ሲስተም አማካኝነት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ የዳኝነት አገልግሎቶች ለተገልጋዮች ተደራሽ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል ብለዋል፡፡

እንደ ሥራ አስፈጻሚዋ ገለጻ፤ ስምምነቱ በሁለቱ ተቋማት መካከል የአቅም ግንባታ፣ ሥልጠና፣ የዕውቀት፣ የክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ያስችላል:: የመሠረተ ልማቱ ግንባታ ሲጠናቀቅ፣ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጠውን የዳኝነት አገልግሎት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ አስተማማኝና ተደራሽ፣ ባለድርሻ አካላት በቀላሉ መረጃ የሚያገኙበት እንዲሆን ያስችላል::

በፍትሕ ሥርዓቱ ግልጸኝነትን ለማስፈንና ዜጎች በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ እምነት እንዲኖራቸው ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው አስረድተዋል፡፡

የዲጂታል መሠረተ ልማት ግንባታ ሲጠናቀቅ ዜጎች የፍርድ ቤት ጉዳይ መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል ያሉት ፍሬህይወት፤ የመረጃዎቻቸው ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን፣ ግልጽ የሆነ የፍትሕ አሠራር እንዲሰፍን እንደሚደርግ ተናግረዋል፡፡

የፍርድ ቤት ጉዳይ መረጃዎችን ለመመርመር፣ ውጤታማና ጥራት ያለው የፍትሕ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚያደርግ አብራርተው፤ ኢትዮ ቴሌኮም የዲጂታላይዜሽን ተግባር አጠናክሮ በመቀጠል የዲጂታል ኢትዮጵያን ራዕይ እውን ማድረጉንና የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጡን አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

# በመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች ላይ ጥቃት በመፈጸም ሁከት ለመቀስቀስ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ቡድኖች በቁጥጥር ስር ዋሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ፣ በባህርዳር፣ በአዳማና በድሬዳዋ ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮችን ኢላማ ያደረገ ጥቃቶች በመፈጸም አገራዊ ሁከትና ብጥብጥ ለማስነሳት ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ቡድኖች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረኃይል አስታወቀ፡፡

የጋራ ግብረኃይሉ በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በአማራና በሌሎች ክልሎች ውስጥ መቀመጫቸውን ያደረጉ እንዲሁም አዲስ አበባ ጭምር የሚገኙ ምሁራን፣ የሚዲያ ባለቤቶችና አክቲቪስቶችን ያካተተ ህቡዕ መዋቅር በምስጢር ሲንቀሳቀስ እንደነበር ተደርሶበታል።

ዶክተር ወንደሰን አሰፋ፣ ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይ አውግቸው፣ ፕሮፌሰር ማዕረጉ ቢያበይን፣ ዶክተር መሠረት ወርቁ፣ ተስፋዬ ወ/ማርያም፣ ተስፋዬ የኋላሸት ፋሲል ሰለሞን ልመንህ ከተማና መንበረ የተባሉ ግለሰቦችም በህቡዕ አደረጃጀቱ ሲሳተፉና ሲያስተባብሩ በቁጥጥር ስር ውለዋል።


አገራዊ ለውጡን ለማስቀጠል በከፍተኛ የባለቤትነትና የኃላፊነት መንፈስ የሚንቀሳቀሰውን ሰፊውን የአማራን ሕዝብ የማይወክሉት እና አሁን የተፈጠረው አንጻራዊ ሰላም ያልተመቻቸው እነዚህ ጽንፈኛ ቡድኖች ኅብረተሰቡ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ጭቆና ውስጥ ይገኛል የሚል ቅስቀሳ በማድረግ በሃይማኖት፣ በብሔር እንዲሁም ከእኛ ውጪ አገሪቷን ሌላ ማስተዳደር የለበትም በሚል የፖለቲካ ፅንፈኝነት ዓላማ ዙሪያ ደጋፊዎችን ለማሰባሰብ እየሞከሩ መሆኑን መግለጫው አመልክቷል፡፡

በዚህም ሕዝቡን ነፃ እናወጣለን የሚል የአመጽ እንቅስቃሴ ለማካሄድ ሲደራጁና አገሪቱን ዳግም ወደነበረችበት ቀውስ ለመመለስ ሲንቀሳቀሱ እንደነበርም ጠቁሟል።

ይህንን አላማቸውን ከግብ ለማድረስ በአማራ ክልል ውስጥ በሁሉም ስፍራዎችና በአዲስ አበባ እንዲሁም በአገሪቷ በሚገኙ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን በአካባቢዎቹ ከሚኖሩ የብሔሩ ተወላጆች ጋር አስተሳስሮ የማደራጀት ሥራዎች ሲሰሩ እንደነበር መግለጫው አስታውቋል።

በተቀናጀ መልኩ ህቡዕ ወታደራዊ ክንፍ በማደራጀት በጦር መሣሪያ የታገዘ የከተማ ላይ ጥቃት የመፈፀም እቅድ እንደነበራቸው፤ በተለይ በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት ባለስልጣናት ላይ ጥቃት በመፈፀም ሕዝቡን የማሸበር ተልዕኮ አንግበው ሲንቀሳቀሱ መቆየታቸውን የጋራ ግብረኃይሉ መግለጫ ጠቁሟል፡፡

ከላይ በተገለጹት ህቡዕ አመራሮች የተዋቀረው የአዲስ አበባው የአደረጃጀቱ ክንፍ በየክፍለ ከተማው ለዘረጋው መዋቅሩ በርካታ የተለያዩ የነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያዎች፣



ተቀጣጣይ ፈንጂዎችና ቦምቦችን ወደ ከተማዋ ማስገባቱንም መግለጫው አስታውቋል፡፡

ከእነዚህ ውስጥ ግዛት የተባለ ባህርዳር ዙሪያ ቁንዝላ አካባቢ መቀመጫውን ያደረገና በአዲስ ውስጥ ለሚገኘው ህቡዕ ክንፍ የተለያዩ ሎጀስቲክስ የሚያቀርብ ግለሰብ በርካታ የእጅ ቦምብ በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች ለሚገኙት የቡድኑ አባላት እንዲያስረክብ አቅጣጫ የተሰጠው ቢሆንም፤ በተደረገው ክትትል በቁጥጥር ስር እንዲውል ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም አዲስ አበባ ጣፎ አካባቢ በሚገኝ የቡድኑ አስተባባሪ በሆነው ዳዊት አባቡ ቢተው እና አዲስ አበባ ካራ አሎ አካባቢ ነዋሪ በሆነው ታደሰ ወይነው ተሰማ ላይ በተደረገው ክትትል የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችና የወታደር ዩኒፎርሞች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ መደረጉን ግብረኃይሉ ለመገናኛ ብዙኃን በላከው መግለጫ አመልክቷል፡፡

ሙሉቀን ወንዴ ቢተው፣ ቴዎድሮስ ተሾመ አየነውና ሌሎችም በህቡዕ አደረጃጀቱ በነበራቸው ተሳትፎ መያዛቸውን ጠቁሟል፡፡

በህቡዕ አደረጃጀቱ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሌሎች ተጠርጣሪዎችን በቁጥርር ስር የማዋሉ ተግባር በተቀናጀ መንገድ መቀጠሉን ያመለከተው የጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረኃይሉ መግለጫ፤ በቀጣይ ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ወቅታዊ መረጃዎችን ለኅብረተሰቡ ተከታትሎ እንደሚያቀርብ አስታውቋል፡፡

# ባለድርሻ አካላት ለትምህርት ጥራት የወጡ ሕጎች እንዲተገበሩ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ተጠየቀ

**ሞገስ ተስፋ**

ቢሾፍቱ፡- የትምህርትን ጥራት ለማስጠበቅና ለመተግበር የወጡ ሕጎችና መመሪያዎችን ለማስፈጸም የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ በመሆኑ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አሳሰበ። ባለስልጣናቱ በተቀናጀ የትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ፣ የፈቃድ እድሳትና የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር አድርጓል።

በኢፌዴሪ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን የተቋማት ቁጥጥር፣ ኢንስፔክሽንና የትምህርት ማስረጃና ማረጋገጫ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ቾሩጌታ ገነነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በባለስልጣኑ ባለፉት ሰባት ወራት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ጥራትን መሠረት ያደረጉ ናቸው። ይህም ከዚህ በፊት የነበሩ ስታንዳርዶችን እና ደረጃን የማሻሻል ሥራዎች ጊዜውን በሚመጥን መልኩ የማጥራት ሥራን ያካተተ ነው።

ከዚህ በፊት እንደ ችግር ሲነሳ የነበረው የጥራት ጉዳይ ስለነበር አሁን ላይ አገሪቱ የምትፈልገውን ብቁና ችግር ፈቺ የሆነ የተማረ የሰው ኃይል እንዲኖራት የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅ የሚያስችል ስታንዳርድን የማሻሻል ሥራ መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ም/ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለዚህም በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ ስታንዳርድን ማሻሻል ዋናው መለኪያ ተፈጻሚነታቸውን የማስፋት ሥራ ነው። ለዚህም የፈቃድ አሰጣጥ ስታንዳርዶችን ማሻሻልና መተገበር፣ የቁጥጥር፣ የእውቅና ሥራ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል።

አሁን ላይ አዳዲሶቹ ስታንዳርዶች ሥራ ላይ እስከሚወሉ ነባሩ ስታንዳርድ ትግበራ ላይ እየዋለ መሆኑን የገለጹት አቶ ቾሩጌታ፣ ከዚህ በፊት በትምህርት ጥራት ላይ አገር የገባችበትን አሳሳቢ ሁኔታ በሚመጥን መልኩ አልተሠራም። ይህን ችግር ለመቅረፍ ስታንዳርዶች ወቅቱን በዋጀ መልኩ ወጥተው እንዲተገበሩ እየተሠራ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ እስካሁን 360 የሚሆኑ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ፈቃድ ወስደው እየሠሩ ነው። ፈቃድና እውቅናን በአንድ ላይ የመጠቀምና ተቋማት ለተመዝጋቢዎች የሚሰጡት የማስታወቂያ መረጃ መታረም አለበት። ሆኖም በኢትዮጵያ እስካሁን እውቅና የተሰጠው ተቋም የለም።

የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ባለስልጣኑ ስታንዳርዶችን አውጥቶ እየሠራ ነው። ነገር ግን ብቻውን የሚሠራው ተግባር ጥራትን ማስጠበቅ አይችልም። ስለሆነም የሚወጡ ሕጐችንና መመሪያዎችን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊሠሩበት ይገባል ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደሮች፣ ወላጆችና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ቁልፍ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

ባለስልጣኑ በተቀናጀ የትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ፣ የፈቃድ እድሳትና የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቢሾፍቱ ምክክር አድርጓል።

የምክክር መድረኩ ተሳታፊዎች የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ድንበርና ወሰን አያስፈልገውም። መንግሥት በትኩረት ሊሠራ ይገባል። በትምህርት ጥራት ላይ የማይመለከተው ተቋምና ዜጋ ስለሌለ በትምህርት ላይ የሚነግዱ አካላትን በጋራ መከላከል ይገባል ብለዋል።

# ከድርቅ በኋላ የሚከሰቱ የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከል ቅድመ ጥንቃቄ እየተደረገ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ድርቅ በተከሰተባቸው አንዳንድ አካባቢዎች ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል የቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ እንደገለጹት፤ የግብርና ሚኒስቴር ድርቁ በተከሰተባቸው ቦታዎች ላይ ሊነሱ የሚችሉ የእንስሳት በሽታዎች እና ሌሎች ችግሮችን አስቀድሞ መከላከል የሚያስችል ሥራ እየሠራ ነው፡፡

በዋናነትም ከእንስሳት ጤና እና ከእንስሳት መኖ ጋር ተያይዞ ያለውን ሁኔታ በየጊዜው የሚያሳውቅ ቡድን ተዋቅሮ በሁሉም ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ተልኳል ብለዋል፡፡

ድርቅ ላይ የቆዩ አካባቢዎች ከብዙ ጊዜ በኋላ ዝናብ ሲዘንብ እፎይታ ቢያገኙም ጉዳት ማስከተሉም አይቀሬ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ድርቅ ላይ የቆዩት እንስሳት ሁኔታዎችን መቋቋም እንደሚከብዳቸውና ዝናቡን ተከትሎም የተለያዩ የእንስሳት በሽታዎች የመከሰት ዕድላቸው የሰፋ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር ፍቅሩ ገለፃ፤ ድርቁ ከተከሰተ በኋላ በመኖ እጥረት ሰውነታቸው ለተጎዱ እንስሳት መድኃኒቶች እየተገዙ ነው፡፡ በተመሳሳይ ከድርቅ በኋላ ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት ሊከሰቱ ለሚችሉ የእንስሳት በሽታዎች ክትባቶች እና መድኃኒቶች እየተገዙ ነው፡፡

እስካሁን ከየትኛውም ክልል እንዲሁም እኛ ካስቀመጥናቸው ቡድኖች ምንም የእንስሳት በሽታ ተከስቷል የሚል ጥቆማ አልደረሰንም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ግን ሊከሰቱ ይችላሉ ብሎ ያሰባቸው ችግሮችን ለይቶ ቀድሞ ለመከላከል እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በኦሮሚያ፣ ደቡብና ሶማሌ ክልሎች የተከሰተው ድርቅ በእንስሳት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ከዚህ ቀደም ድጋፍ መደረጉን ጠቁመውም፤ ለክልሎች የተደረገው የገንዘብ ድጋፍ እንደ ክልሎቹ ጥያቄ እና እንዳለባቸው ችግር የመኖ፣ የመድኃኒት እና ክትባት መግዣ እንዲውል እየተደረገ መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

# ባለሥልጣኑ በጅማና ሀዋሳ ከተሞች የቡና ማቀነባበሪያ ማዕከላትን ሊከፍት ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ቡናን በማዘጋጀት በቀጥታ ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚረዱ የማቀነባበሪያ ማዕከላትን በጅማና ሀዋሳ ከተሞች ሊከፍት መሆኑን የኢትዮጵያ የቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ የቡናና ሻይ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ኡመር በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ባለሥልጣኑ በአዲስ አበባ ብቻ የነበረውን የቡና ማቀነባበሪያ ማዕከላትን በክልል ከተሞች በማስፋት በቀጥታ ወደ ውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ተጨማሪ ሁለት ማዕከላትን በጅማና ሐዋሳ ሊከፍት ነው።

ባለሥልጣኑ በመጪው መጋቢት 28 ቀን 2015 ዓ.ም በጅማ ከተማ እንዲሁም በሚያዝያ 3 ቀን 2015 ዓ.ም በሐዋሳ ከተማ በዘመናዊ መልክ የተገነቡትን የቡና ማቀነባበሪያ ማዕከላት በይፋ ያስመርቃል ብለዋል።

ባለሥልጣኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በቡና ዘርፍ እየታየ ያለውን የገበያ ችግር ለመፍታት ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን አከናውኗል ያሉት አቶ ሻፊ፤ የቡና ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ዘመናዊ ማዕከላትን ማስፋፋት ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

አቶ ሻፊ እንዳስታወቁት፤ ከዚህ ቀደም ቡና በስፋት በሚመረትባቸው ስፍራዎች የቡና ማቀነባበሪያ ማዕከላት ባለመኖራቸው የተለያዩ ኪሳራዎች ተከስተዋል።

ዘመናዊ ማዕከላት በክልል አካባቢዎች ባለመስፋፋታቸው የቡና ምርት በስፋትና በፍጥነት ተመርቶ ወደ ውጭ ገበያ እንዳይቀርብ፣ የቡናው ጥራት እንዲጓደል ከማድረጉ ባለፈ ከተመረተበት ስፍራ ተጭኖ ወደ አዲስ አበባ እስኪመጣ በጊዜና በገንዘብ ተጨማሪ ወጪ እየጠየቀ መሆኑን አስታውሰዋል።

ያልተቀሸረ ቡና ወደ አዲስ አበባ ተጭኖ ከሚመጣ ይልቅ እዚያው በተመረተበት አካባቢ ሂደቱን ጠብቆ በተቀነባበረ መንገድ ቢታሸግ ከጥራት አንጻር በውጭ ገበያ ላይ ተመራጭነቱ እንደሚጨምር አስረድተዋል።

ችግሩን ለመቀነስ ዘመናዊ የማቀነባበሪያ ማዕከላቱ መገንባት አስፈልጓል ያሉት አቶ ሻፊ፤ ማዕከላቱ ጥራት ያለው ቡና በማቀነባበር ወደውጭ ገበያ ለመላክ መሆኑን ጠቁመዋል።

ማዕከላቶቹ ወደሥራ ሲገቡ ሕገወጥ የገበያ ሰንሰለቶች እንዲያጥሩ በማድረግ ቡና በቀጥታ ከአቅራቢው ወደላኪው እንዲደርስና አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ያግዛል ብለዋል።

ማዕከላቱ የቡና ምርት ጥራት እንዲጠበቅ፤ በአቅራቢውና በላኪው መካከል ፍትሀዊ ተጠቃሚነትና መተሳሰብ እንዲሁም ብዛት ያለውን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ እንደሚረዱ ገልጸዋል።

የቡና መቀነባበሪያ ማዕከላቱ ቡናን ከአርሶአደሩ በመቀበል ፈልፍሎ፣ ቆልቶና በዘመናዊ መልዕኩ አሽጎ ለዓለም ገበያ በማቅረብ የአገሪቷን ኢኮኖሚ ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ወሳኝ ሚና እንደሚወጡ ይጠበቃል ሲሉ አቶ ሻፊ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ የቡናና ሻይ ባለሥልጣን አዲስ አበባና ድሬዳዋ ላይ ዘመናዊ የቡና መቀነባበሪያ ማዕከላት ያሉት ሲሆን፤ በ2016 ዓ.ም በጊምቢና ነቀምት ከተሞች ተጨማሪ ማዕከላት ለመገንባት ዕቅድ መያዙን አቶ ሻፊ ተናግረዋል።

# «በአገሪቱ የተሻለ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይህንንም ሁሉም ሊተባበር እና ሊደግፈው የሚገባ ተግባር ነው።

ባሳለፍናቸው የፈተና ጊዜያት የተለያዩ አካላት ከበጎው ይልቅ ክፉውን ለማንጸባረቅ ቅድሚያ ሰጥተዋል ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ የተለያዩ የማህበራዊ ገጾች ላይም መጥፎ ዜናዎች ተቀባይነት ሲያገኙና ቀድመው ምላሽ ሲሰጥባቸው ተስተውሏል ብለዋል፡፡

ስለ ሰላም፣ ስለአገር ግንባታ እና ስለአብሮነት የተሠሩ ሥራዎች ግን ተመልካችም ሰሚም ያጡበት ጊዜ እንደነበር ገልጸው፤ ይህም ትልቁ ችግራችን ነው ብለዋል። ስለሰላም መሠራትም ሆነ መዘመር ያለበት አጋጣሚዎችን እየጠበቁ አይደለም፣ ሰላም የምንጊዜም ሥራ ነው ሲሉ አክለዋል።

ኢትዮጵያውያን አብሮነት፣ መከባበር፣ እንግዳ ተቀባይነት እና ስለሰው የሚጨነቅ ማህበረሰብ አለን ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ አሁን ግን ወንድም ወንድሙን የሚያጠቃበት ጊዜ ላይ መድረሳችንን ባለፉት ጊዜያት አይተነዋል ብለዋል። ይህም ፍጹም ትክክል አለመሆኑን አብራርተዋል፡፡

እየጎዳንና እያጠቃን ያለው የውጭ ኃይል አይደለም ብለው፤ ባሳለፍናቸው ጊዜያት ውስጥ ያሳለፍናቸው ፈተናዎች እኛው በእኛው የፈጠርናቸው ናቸው ሲሉ ገልጸዋል። ያሉብንን ችግሮች የማለፍ ሥራ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው ሲሉ አሳስበዋል።

በተለይ ኃይማኖቶች ለግጭት መንስኤ ሊሆኑ አይገባም ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ በኃይማኖት የሚነሱ የሙብት ጉዳዮች ላይ የጎደሉ ነገሮች ካሉ በመነጋገር መንግሥት እልባት እየሰጠ ለግጭት መንስኤ እንዳይሆኑ መቋጨት ያስፈልጋል ብለዋል።

በመጨረሻም የኃይማኖት አባቶች መንግሥት ሲያጠፋ እዚጋ ስህተት አለ ብሎ በጋራ ለማረም መጣር ይኖርባቸዋል። ከዚህ ባለፈም መንግሥት አገሪቱ እንድትረጋጋ በሚያደርጋቸው ጥረቶች አብሮ መቆም እና ከፊት ሆኖ መምራት የኃይማኖት አባቶች እና የቤተ እምነቶች ኃላፊነት እና ግዴታ ነው ብለዋል፡፡

# የኢፕድ የሥልጠና ማዕከል ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዙር ሥልጠና መከፈቻ መርሃግብር ላይ እንደተናገሩት፤ የኢፕድ የሥልጠና ማዕከል ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በመጀመሪያ ዙር የሰጠው ሥልጠና በተቋሙ ባለሙያዎች ላይ ሙያዊ ለውጥ አምጥቷል። በባለሙያዎቹ ላይ የተገኘውን ተጨባጭ ለውጥ የበለጠ ለማጠናከር በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሁለተኛ ዙር ሥልጠና እየወሰዱ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ወቅታዊ፣ አገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ መረጃዎችን በትክክልና በፍጥነት ለሕዝብ እያደረሰ ያለ የሚዲያ ተቋም ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ ድርጅቱ በዘርፉ ያካበተውን ልምድ የሥልጠና ማዕከል በማደራጀት ለተቋማት የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች መስጠቱ የሚያስመሰግን ተግባር ነው ብለዋል።

ኢፕድ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሥራዎችን ለሕዝብ ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል። ይህን አጠናክሮ መቀጠል አለበት ያሉት አቶ መላኩ፤ ድርጅቱ በዘርፉ ያካበተውን ልምድ የአገልግሎቱ ባለሙያዎች በትኩረት በመቀበል ወደተግባር እንዲቀይሩ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው፤ ድርጅቱ በሚዲያ ዘርፍ ያካበተውን ልምድ ለሌሎች ተቋማት ለማስተላለፍ የሥልጠና ማዕከል ከፍቶ ከ22 በላይ በሆኑ ዙሮች ለፌዴራል እና ለክልል ተቋማት የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎችና ጋዜጠኞች ሥልጠና መስጠት ችሏል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለሙያዎች የሁለተኛ ዙር ሥልጠና ለመውሰድ ስለመጡ አመስግነው፤ ድርጅቱ በሚዲያ ዘርፍ ያካበተውን ልምድ ለሌሎች ተቋማት ለማስተላለፍ የሥልጠና ማዕከል ከፍቷል፤ በማዕከሉ በርካታ ተቋማት ሰልጥነዋል ሲሉ ገልጸዋል።

በሥልጠና ማዕከሉ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለሙያዎች የወሰዱት ሥልጠና ውጤታማ ሆኖ ደግመው ሁለተኛ ዙር ሥልጠና ለመውሰድ በመምጣታቸው ደስታ ተሰምቶናል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የዛሬዎቹ ሠልጣኞችም የሚሰጣቸውን ተግባር ተኮር ሥልጠና በትኩረትና በንቃት በመከታተል ተጨማሪ ተጨባጭ ለውጥ ለመሥሪያ ቤታቸው ማስገኘት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት መብራት በሌለባቸው እና ጦርነት በነበረባቸው አካባቢዎች በድጋሚ የመብራት አገልግሎት እንዲያገኙ ያደረገበት መንገድ የሚደነቅ ነው ብለው፤ ኢፕድ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሥራዎችን በፍጥነት ለሕዝብ ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል፤ ይህንንም አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሥልጠና ማዕከሉ የተለያዩ የፌዴራል፣ የክልልና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቋማት የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ ባለሙያዎችን በአዲስ አበባ እና በክልሎች አሰልጥኖ ማስመረቁ ይታወሳል።

# ምክር ቤቱ በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የምክር ቤት አባሉ ያለመከሰስ መብታቸው የነሳው የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ወቅት የመንግሥትን የግዢ መመሪያ ሳይከተል በተደረገ የመኪኖች እና የማሽነሪዎች ግዢ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፣ ያለጨረታ ሥራዎችን ለተቋራጮች ከመስጠት ጋር በተያያዘ የሙስና ወንጀል በመጠርጠራቸውም እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡

ዶክተር ጫላ ዋታ በሙስና ወንጀል በመጠርጠራቸው ምክንያት ያለመከሰስ መብታቸው እንዲነሳ ፍትሕ ሚኒስቴር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን በመጠየቁ የውሳኔ ሀሳብ መቅረቡን የምክር ቤቱ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ እፀገነት መንግሥቱ ገልጸዋል።

የምክር ቤቱ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ዝርዝር ውይይት መደረጉንና ያለመከሰስ መብታቸው እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበባቸውን የምክር ቤት አባል ጠርቶ ማነጋገሩንም አመልክተዋል።

የፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴር የአባሉ ያለመከሰስ መብት እንዲነሳ በጠየቀው መሠረት የምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ማጣራት ማድረጉን ገልጸ፤ በዚህም አባሉ የመንግሥት የግዢ ሕግ ከሚፈቅደው አሠራር ውጪ የውስጥ ገቢ ማስገኛ በሚል «ቢኤችዩ ኮንሰልቲንግ ኢንጂነርስ ጀነራል ሌቭል ዋን» የተባለ አማካሪ ድርጅት በማቋቋም በስማቸው ንግድ ፍቃድ ማውጣታቸውን ተገንዝቧል፡፡

የቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ ቋሚ ኮሚቴው ምርመራ ማድረጉን የገለጸ ሲሆን በተደረገው ማጣራት የብር 195 ሚሊዮን 52ሺ812 ከ81 ሳንቲም የሚያወጡ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች ለ9 ተቋራጮች ከመንግሥት የግዢ አዋጅ እና መመሪያ ውጪ ክፍያ መፈጸሙን እንዲሁም ዋጋቸው 116 ሚሊዮን ብር የሆኑ 14 ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች በግል ተቋራጭ ድርጅት ስም ግዢ መፈጸሙን አረጋግጧል፡፡

በተጨማሪም ተሽከርካሪና ማሽነሪዎቹ በዩኒቨርሲቲው ገንዘብ የተገዙ ቢሆኑም በግል ተቋራጮች ድርጅቶች ስም እንዲሆኑ መደረጉንና ተሽከርካሪዎቹ እና ማሽነሪዎቹ የተገዙበት ዋጋ እጅግ የተጋነነ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በዚሁ መሠረት ዶክተር ጫላ «የተጠረጠሩበትን ወንጀል ለመፈጸማቸው በቂ አመላካች ነገር መገኘቱን አረጋግጧል» ብለዋል።

ቋሚ ኮሚቴው ለድርጊቱ መፈጸም በቂ አመላካች ሁኔታዎች መኖራቸውን በማረጋገጡም ለምክር ቤቱ የዶክተር ጫላ ዋታ ያለመከሰስ መብት እንዲነሳ ባቀረበው መሠረት ምክር ቤቱ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ከመረመረና አስተያየቶችን ከሰጠ በኋላ በአንድ ድምጸ ተአቅቦ በአብላጫ ድምጽ የምክር ቤቱን አባል ያለመከሰስ መብት አንስቷል።

በሌላ በኩልም ምክር ቤቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሹመትንም መርምሮ አጽድቋል፡፡

የውሳኔ ሀሳቡን ያቀረቡት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጂጌ፤ ሹመቱ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 81 (2) መሠረት መቅረቡን በማብራራት የተሿሚዎቹ የትምህርት እና የሥራ ልምድ ዙሪያ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡

የምክር ቤት አባላትም ተሿሚዎቹ ባላቸው የትምህርትና የሥራ ልምድ ለቦታው ብቁ ናቸው ሲሉ ድጋፋቸውን ገልጸዋል፡፡

በዚህም መሠረት በውሳኔ ቁጥር 14 እና 15/2015 ዓ.ም በሁለት ድምጸ-ተአቅቦ በአብላጫ ድምጽ ወይዘሮ ሌሊሴ ደሳለኝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ወይዘሮ ዘሀራ ኡመር አሊ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ተሹመዋል። በምክር ቤቱ ፊት ቀርበውም ቃለ-መሀላ ፈጽመዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## በሳውዲ አረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ዜጎችን ለመታደግ የተደረገው ጥረት የሚደነቅ ነው

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተደነገገውን የሰዎች በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት ሀገራችን ኢትዮጵያ የተቀበለችውና በህገ መንግስቷም ያረጋገጠችው ነው፡፡ በዚሁ መሰረትም ዜጎች ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍሎች በህጋዊ መንገድ እየተንቀሳቀሱ የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን ያከናውናሉ።

ከዚሁ በተቃራኒ በህገ ወጥ መንገድ ድንበር አቋርጠው እና ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው የሚሰደዱትም ዜጎች አሉ፡፡ በተለይም ወደመካከለኛው ምስራቅ ሳውዲ አረቢያ፤ ሊባኖስ፤ ኩዌት፤ ሶርያ፤ የተባበሩት አረብ ኢምሬት የሚጓዙ ቁጥራቸው ከፍተኛ እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ።

በህገ ወጥ ስደት ምክንያት ደግሞ ዜጎችን ለመከራና ስቃይ ይዳርጋል፡፡ ክብርንና ሕሊናን የሚያዋርድ መከራን ከመቀበል ጀምሮ እስር፣ እንግልትን፣ የጉልበት ብዝበዛ፤ አካላዊና ስነልቦናዊ ጥቃት፤ አስገድዶ መደፈር፤ ሞትን ጭምር መጋፈጥን የሚጠይቅ ነው።

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከኢትዮጵያ በየአመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በህገወጥ መልኩ ከሀገር ይወጣሉ፡፡ አብዛኞቹም ስደተኞች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ያላጠናቀቁና ከገጠራቱ የሀገሪቱ ክፍል የሚፈልሱ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ በህገ ወጥ ደላሎች ፤ ‹‹የተሻለ ሕይወት፤ ስራና ኑሮ ታገኛላችሁ›› በሚሉ ተታልለው ለህገ ወጥ ስደት የተዳረጉ ናቸው፡፡

እነዚህ ዜጎች በየደረሱባቸው ሀገራት ሰብዓዊ ክብራቸው ከመነካቱም በላይ በርካታ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡ አካል መጉደል፤ መደፈር፤ የመጓጓዣ ሰነዶች መነጠቅና ባልተገባ መልኩ በጠባብ ክፍል ውስጥ መታጎር/መታሰር የመሳሰሉት አስከፊ ድርጊቶች ይፈጸሙባቸዋል፡፡ የተፈጸሙባቸውን አሰቃቂ ድርጊቶች አሳውቆ ፍትህ ማግኘት እንኳን የሚታሰብ አይደለም፡፡

ከአገራዊ ለውጡ ማግስት ሰው ተኮር ስራ እየሰራ ያለው እና በውጭ ግንኙነት ስራውም ለዜጎች ክብር ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሰራው የኢትዮጵያ መንግስትም እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባትና የዜጎቹን ዋስትና ለማረጋገጥ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በመመደብ እና ባለሙያዎችን በማሰማራት ጭምር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ዜጎች ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ ረጅም ርቀት ተጉዟል፡፡ በተለያዩ ጊዜዎችም ዜጎችን ከዚህ ችግር እንዲወጡ ያስቻላቸውን ርምጃ ወስዷል፡፡ በቅርቡም ዜጎችን በስደት ከሚደርስባቸው ችግር ለመታደግ በወሰደው ርምጃም ከፍ ያለ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

በተለይም ካለፈው አንድ አመት ጀምሮ በሕገ ወጥ መንገድ ከአገር ወጥተው በሳውዲ ዓረቢያ በእስር ላይና በማቆያ ቦታዎች በችግር ውስጥ የነበሩ ዜጎችን ወደ አገራቸው ለመመለስ ያደረገው ጥረት እጅግ ፈታኝ ቢሆንም፤ ውጤቱ ግን ለዜጎች ያለውን ክብር በተጨባጭ ያመላከተ ነው።

መንግስት መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም ሕገ ወጥ ስደተኞችን የመመለሱ ተግባር ሲጀመር በሳውዲ ዓረቢያ በእስርና በማቆያ ጣቢያዎች የሚገኙ 102ሺ ዜጎችን ለመመለስ አቅዶ የነበረ ቢሆንም፤ ሰሞኑን ይፋ በሆነው መረጃ ግን ከ131 ሺህ በላይ ዜጎች ወደአገራቸው መመለስ ተችሏል።

እነዚህ ዜጎች በተለይ በማቆያ ጣቢያዎች ውስጥ ለበርካታ እንግልትና ስቃይ ተዳርገው የነበሩ ከመሆናቸውም በላይ ብዙዎችም ወደ ሀገራቸው የሚመለሱበት ገንዘብ ጭምር የሌላቸው መሆናቸው የነበሩበትን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን የመመለሱን ስራ አስቸጋሪና ከፍ ያለ ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ያደረገ ነበር፡፡

መንግስት የሁኔታውን አስከፊነትና የሚጠይቀውን ቁርጠኝነት በአግባቡ በመረዳት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን 16 መንግስታዊ ተቋማት በማስተባበር፤ ከ520 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ በ131ሺ በላይ ዜጎችን ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ አድርጓል። ከሳውዲ አረቢያ በተጨማሪም በተለያዩ አገራት በተመሳሳይ ችግሮች ውስጥ የነበሩ ስምንት ሺ ዜጎችን የመመለስ ሥራም አከናውኗል፡፡

መንግስት ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ያከናወነው ይህ ተግባር ለዜጎቹ እና ለሀገር ያለውን ከፍተኛ ከበሬታ በተጨባጭ ያሳየ፤ ለዜጎቹ ከሚቆረቆር አንድ መንግስት የሚጠበቅ፣ ሊበረታታ እና እውቅና ሊሰጠው የሚገባ፤ ከዛም በላይ የሚደነቅ ተግባር ነው፡፡

በተለይም ከለውጡ ወዲህ በተዘረጋው ዜጋ ተኮር ፖሊስ አማካኝነት እየተከናወነ ያለው ስራ የዜጎችን በሕይወት የመኖር ዋስትና ጭምር እያረጋገጠ የሚገኝ በመሆኑ፤ መንግስት በሳዑዲ አረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ዜጎችን ለመታደግ ያደረገው ጥረት የሚደነቅ ነው፡፡ በቀጣይም ይሄው ተግባር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሚበረታታው የመንግሥት ሠራተኞችን የቤት ባለቤት የማድረግ ጥረት

**ሜሳት ኢያሱ**

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን በተለይም የመንግሥት ሠራተኞችን ሕይወት ፈታኝ ካደረጉ ጉዳዮች ግንባር ቀደሙ የመኖሪያ ቤት ችግር ነው።የቤት ኪራይ የከተማዋን ኢኮኖሚ እስከመዘወር፣ በከተማዋ የመኖር እና ያለመኖር ሁኔታን እስከመወሰን እንደደረሰ ሁላችንም የታዘብነው ሐቅ ነው።

መጠለያ ምግብና ልብስ ለሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ናቸው፡፡ በድሮው አስተሳሰብ አንድ ሰው መኖሪያ ቤት አለው ሲባል ከሶስቱ መሰረታዊ ፍላጎቶች አንዱን አሟልቷል የሚል ትርጉም ይሰጠው ነበር፡፡ አሁን ግን አንድ ሰው በተለይም ሰፋ ባለ ከተማ ውስጥ ቤት አለው ከተባለ የሚሰጠው ትርጉም ማረፊያውን ወይም መውደቂውን አመቻችቷል ከሚለው ይልቅ ኢኮኖሚ አፍርቷል ወደሚለው ያመዝናል።

ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ በሚሊዮኖች ደረጃ የሚከራዩ የንግድ ቤቶች አሉ፡፡ በመቶ ሺዎች የሚያከራዩ መኖሪያ ቤቶችም ይገኛሉ። በቤት ኪራይ የሚተዳደረው ሰው በደመወዝ ከሚተዳደረው ሰው የማይተናነስ መሆኑን የምንረዳው አብዛኛው ደመወዝተኛ በአከራዮች ቤት የሚኖር በመሆኑ ነው፡፡

በጥናት የተረጋገጠ መረጃ ባይሆንም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከቤት ኪራይ ጋር በተያያዘ የሚዘዋወረው ኢኮኖሚ ከሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛው ደመወዝ ጋር ሲነጻጻር የሚበልጥ እንጂ የሚያንስ አይመስልም፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆኑን በየአካባቢው ተገንብተው ለንግድ ሥራ የሚከራዩት ሰማይ ጠቀስ ሕንጻዎች፣ ለመኖሪያነት የሚከራዩ ኮንዶሚኒየም ቤቶች፣ በየመንደሩ እየተከራዩ ያሉ ቪላ ቤቶችና ትንንሽ ክፍሎች ናቸው።

በዚህ የተነሳ መኖሪያ ቤት ባላቸው እና በሌላቸው ነዋሪዎች መካከል ያለው የኑሮ ደረጃ የሰማይና የመሬት ያህል ተራርቋል፡፡ በከተማዋ የሚስተዋለው የቤት ኪራይ ውድነት ከዕለት ወደ ዕለት እየናረ ከሚመጣው የሸቀጦች ዋጋ ጋር ተዳምሮ ነዋሪውን ግራ ማጋባቱ የአደባባይ ምስጢር ነው።

የሸቀጦች እና የአገልግሎቶች ዋጋ በጨመረ ቁጥር ቤት አከራዮች በዚያ በኩል ያወጡትን ወጪ በዚህ በኩል ለማካካስ ሲሉ በሚያከራዩት ቤት ላይ ዋጋ መቆለልን እንደ ትክክለኛ መፍትሔ እየተመለከቱ የቤት ኪራይ ዋጋን ሰማይ አድርሰውታል።

እዚህ ጋር አንድ እውነት አለ፡፡ በዓለም አቀፍም ይሁን በአገር አቀፍ ተለዋዋጭ ምክንያቶች የተነሳ የሸቀጦች ዋጋ ሊጨምር ይችላል፡፡ እነዚህን ለዕለት ፍጆታ የምንጠቀማቸውን ሸቀጦች መግዛት የወዴታ ግዴታ ስለሚሆንብን እየተቸገርንም ቢሆን በተባለው ዋጋ ከመግዛት ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖረንም፡፡ ከዚህ አንጻር የሸቀጦች ዋጋ መጨመር ምክንያታዊ ነው ሊባል ይችላል፡፡

የሸቀጦች ዋጋ በጨመረ ቁጥር አከራዮች ያንን ለማካካስ በቤት ተከራዮች ላይ የሚጭኑት ጭማሪ ግን ምክንያታዊ አይደለም፡፡ ለምን ቢባል የዋጋ ንረቱ በአከራዩም በተከራዩም ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ተመሳሳይ ሆኖ ሳለ ቤት አከራዮች በሸቀጦች ላይ ዋጋ በተጨመረ ቁጥር እነርሱም በፊናቸው በሚያከራዩት ቤት ላይ ዋጋ እየጨመሩ የሕዝቡን ኑሮ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ማድረጋቸው ተገቢነት የለውም።

ቤት አከራዮች፣ ነጋዴዎች እና አገልግሎት ሰጪዎች አንዳንድ ጊዜ በምክንያት አንዳንድ ጊዜም ያለበቂ ምክንያት በሚያደርጉት ረፍት የሌለው የዋጋ ጭማሪ የኑሮ ውድነቱ እንዲጨምር አድርጎታል፡፡ ከሁሉም አቅጣጫ የሚሰነዘረው ዱላ የሚያርፍበት ደግሞ የወር ደመወዝ ጠብቆ በሚኖረው የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኛ ላይ ነው።

ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ አንዲት ሶስት በአራት የሆነች ክፍል በአማካይ ከአራት እስከ አምስት ሺህ ብር ትከራያለች፡፡ አንድ ባለ አንድ መኝታ ኮንዶሚኒየም ቤት (እንደ የቦታው ሁኔታ ያለው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ) ከአስር እስከ አስራ ሁለት ሺህ ብር ይከራያል፡፡

አንድ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ በሥራ ዓለም የተሰማራ ጀማሪ የሲቪል ሰርቪስ ደመወዝተኛ ደግሞ በአማካይ ከሶስት እስከ አምስት ሺህ ብር ሲከፈለው ነባር ሰራተኛ የሚባለውም ደመወዙ ከአስር እስከ አስራ አራት ሺህ ብር የሚበልጥ አይደለም፡፡

እንግዲህ ደመወዝና የቤት ኪራይ ዋጋ ባልተመጣጠኑባት አዲስ አበባ ከተማ በተለይም መኖሪያ ቤት የሌላቸው የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ምኑን ከምን እያደረጉ እንደሚኖሩ ሲታሰብ ያሳቅቃል።በዚህም ላይ የምግብ፣ የልጆች ትምህርት፣ የአልባሳት፣ የህክምና፣ የትራንስፖርት ወዘተ ወጪዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ።

የሶስት ወርና የአምስት ወር ቅድመ ክፍያ በአንድ ጊዜ ተጠቃሎ እንዲከፈላቸው የሚጠይቁ አንዳንድ ልበ ደንዳና አከራዮች መኖራቸውም አይረሳም፡፡ ውሃ ቀጠነ በሚል ሰበብ ቤት እንዲለቁ የሚገደዱት፤ ጓዛቸውን ጭነው ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት የሚንከራተቱትን እና ለጫኝ እና አውራጆች ሲሳይ የሚሆኑትን ደግሞ ቤቱ ይቁጥራቸው።

መንግሥት የመዲናዋን የመኖሪያ ቤት እጥረት ከግምት በማስገባት የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ገነብቶ ጥያቄዎችን በተወሰነ መልኩ ለመመለስ ባይሞክር ኖሮ ችግሩ ዛሬ ከምናየውም በላይ የከፋ ሊሆን እንደሚችል መረዳት አይከብድም፡፡

ከዚህ ጋር ማንሳት የሚገባን ቁም ነገር አለ። በ1997 ዓ.ም የተጀመረው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ በርካታ ባለእድለኞችን ተጠቃሚ አድርጓል፡፡ ቤቶቹ በችግር ውስጥ ያሉ የመንግሥት ሠራተኞችን ምን ያህል ተጠቃሚ አድርገዋል ከተባለ ግን አጠያያቂ ነው።

የሚገርመው በርካታ ችግረኞች እያሉ የራሳ ቸውን ሕይወት ያልመሰረቱና በቤተሰብ ጥገኝነት ስር ያሉ ወጣቶች ሳይቀሩ የእድሉ ተጠቃሚዎች መሆን ችለዋል፡፡ በሆነ አጋጣሚ የአዲስ አበባ ከተማን መታወቂያ አውጥተው የተመዘገቡና ነዋሪነታቸው ሌላ አገር የሆኑ አካላትም የቤት እድለኛ ሆነዋል፡፡

እንደማንኛውም ዜጋ የእድሉ ተጠቃሚ መሆናቸው አይከፋም ግን በአንገብጋቢ ችግር ውስጥ ያሉ፣ በርካታ ቤተሰብ ይዘው የሚንከራተቱ ፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው፣ ብዙ ዓመታትን አገራቸውን ያገለገሉ አቅመ ደካሞች እያሉ ሌሎች የእድሉ ተጠቃሚ መሆናቸው ብዙ አያሳምንም።

በግል አስተያየቴ ቤት እንደሎተሪ እድለኛ ይድረሰው ተብሎ የሚታደል መሆን የለበትም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ቁልጭ ብለው የሚታዩ የኑሮ እና የአኗኗር ደረጃን ፣ የሥራ ሁኔታን ፣ የቤተሰብ ብዛትን፣ እድሜና የአገልግሎት ዘመንን ወዘተ ከግምት ያስገባ ቢሆን ትክክለኛ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል።

ከሰሞኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመዲናዋ የሚኖሩ የመንግሥት ሠራተኞችን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ አዲስ መርሃ-ግብር አስተዋውቋል፡፡ የመንግሥት ሠራተኛውን የቤት ባለቤት ለማድረግ ከነደፋቸው የተለያዩ አማራጮች አንዱ የማህበር ቤት ነው።

የመንግሥት ሠራተኞች በማህበር ተደራጅተው አቅማቸው በሚፈቅደው ልክ እየቆጠቡ በአጭር ጊዜ የቤት ባለቤት እንዲሆኑ የሚያስችል ነው፡፡ ይህ አሠራር ቤትን እንደሎተሪ በእድል ከመስጠት ይልቅ በትክክል የከፋ ችግር ያለባቸው የመንግሥት ሠራተኞችን ታላሚ ያደረገ በመሆኑ ሊበረታታ ይገባል።

## ፍረዱኝ

# ወደ መፍትሔ ያመራው የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ነዋሪዎችና የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ውዝግብ

ሙሉቀን ታደገ

**ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ ነዋሪዎች አቤቱታ ጋር በተያያዘ ከአስራ አምስት ቀን በፊት ክፍል አንድ ዝግጅታችንን ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ በዚያው ዝግጅታችን በገለፅነው መሠረት እነሆ ዛሬ ክፍል ሁለትን ይዘን ቀርበናል፡፡ በዚህ ክፍል ዝግጅታችንም ከአቤቱታ አቅራቢዎች እና ከሰነዶች የተገኙ የተለያዩ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም ከተለያዩ የቢሮ ኃላፊዎች የተገኙ ምላሾች ተካተው ለአንባቢያን ፍርድ በሚያመች መልኩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

### ከክፍል አንድ ዝግጅት ለትውስታ ያህል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 6፣ በተለምዶ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚገኙ ከ65 በላይ የሚሆኑ አባወራዎች «በራሳችን ወጪ እና መሬት ላይ የሠራነው፣ እንዲሁም ከ60 ዓመት በላይ የኖርንበት ቤታችን ምክንያቱ በውል ባልታወቀ ሁኔታ ‘ቤቱ የመንግሥት ስለሆነ ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማት አስተዳደር ጋር የቀበሌ ቤት ኪራይ ውል ተዋዋሉ’ ተብለን ተገደናል። በራሳችን መሬት እና ወጪ ሠርተን ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በኖርንበት ቤት፣ ሕግ ባለበት አገር፣ እንዴት ከአዲስ አበባ ቤቶች አስተዳደር ጋር የኪራይ ውል ተዋዋሉ እንባላለን? የኢትዮጵያ ሕዝብም መንግሥት ለሕዝብ እንዲያገለግሉ ባስቀመጣቸው ሹመኞች እየደረሰብን ያለውን በደል ተመልክቶ ይፈረደን» ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቤት ብለዋል።

### በአዋጅ ቁጥር 47/67 ትርፍ ቤት የተወረሰባቸው አቤቱታ አቅራቢ

እማሆይ አፀደ ረታ ይባላሉ፤ አሁን ላይ ውዝግብ የተነሳበትን ቤት በራሳቸው የገንዘብ እና የጉልበት ወጪ እንደሠሩት፤ በቤቱም ከአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ እየኖሩበት እንደሚገኙ ይናገራሉ።

እንደ እማሆይ አፀደ ገለጻ፣ በ1967 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 47/67 የደርግ መንግሥት ትርፍ ቤቶችን ሲወርስ ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ማዶ በሚገኘው፣ ቀበሌ 58 እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የነበረ አንድ ቤታቸውን ተወርሰዋል። ቤታቸው ሲወረስ «በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ ከሚገኘው እና በቀበሌ 58 ከሚገኘው ቤት የትኛው ቢወረስ ይመርጣሉ?» ብሎ መንግሥት እንደጠየቃቸው የሚናገሩት ወይዘሮ አፀደ፣ እርሳቸውም በቀበሌ 58 የሚገኘው ቤት ተወርሶ በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ የሚገኘው ቤት እንዲተውላቸው ማድረጋቸውን ያስረዳሉ። ለዚህ በምክንያትነት ያነሱት ደግሞ በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ የሚገኘው ቤታቸው ለባለቤታቸው ሥራ ቅርብ መሆኑን ነው።

የተወረሰው ቤት እስካሁንም ድረስ በቤቶች አስተዳደር ሥር እንደሚገኝ የጠቆሙት እማሆይ አፀደ፤ ስለተወረሰው ቤታቸው የሚያስረዳ ሰነድ እንዳላቸውም አመልክተዋል። የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም ይህንኑ እውነት አረጋግጧል።

ይሁን እንጂ በራሰቸው የገንዘብ እና የጉልበት ወጪ የሠሩትን ቤት በ2002 ዓ.ም አንድ የወረዳ 6 አመራር በማን አለብኝነት ከአሠራር ውጪ «ቤቱ የመንግሥት ስለሆነ የቤት ኪራይ ውል ከመንግሥት ጋር ተዋዋሉ» ብሎ ማስገደዱን ይናገራሉ። ይህም ልክ ያልሆነ እና ሕጋዊ መሠረት የሌለው ነው ያሉት እማሆይ አፀደ፣ በተፈጠረው ችግርም ቤታቸውን ማደስ ባለመቻላቸው አሁን ላይ በእርጅና ዘመናቸው ለከፍተኛ ችግር ተዳርገው እንደሚገኙ ተናግረዋል። በመሆኑም መንግሥት የደረሰባቸውን ችግር ተመልክቶ አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል።

ሌላኛዋ አቤቱታ አቅራቢ ወይዘሮ እህተ ፍርሼ ይባለሉ። የ80 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ ናቸው። በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ለ26 ዓመታት በቋሚነት እና ቁጥሩን በውል ለማያስታውሱት በርካታ ዓመታት ደግሞ በጊዜአዊነት ማገልገላቸውን ይናገራሉ።

እንደ ወይዘሮ እህተ ገለጻ፣ በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሲቀጠሩ የወር ደመወዛቸው አንድ ብር ከአስር ሳንቲም ነበር። የሚያገኟት ገንዘብ ትንሽ ብትሆንም ከሥራ መልስ ወገባቸውን የሚያሳርፉበት ቤት ያስፈልጋቸው ስለነበር ከሚያገኟት ደመወዛቸው ቀንሰው አሁን ላይ ውዝግብ የተነሳበትን ቤት ሠሩ።

እንደ ወይዘሮ እህተ ገለጻ፣ አሁን ያሉበት ቦታ ላይ ከኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ኖረውበታል። የደርግ መንግሥት 47/67 ዓዋጅን ከማወጁ በፊት በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ሁለት ቤቶች ነበሯቸው። በአዋጁ መነሻነት አንዱ ቤታቸው በመንግሥት ተወሰደባቸው። አንደኛው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ሲወረስ የትኛው ቤት በራሳቸው ይዞታ እንዲቀርላቸው እንደሚፈልጉ መንግሥት ጠይቋቸው እንደነበርና እርሳቸውም ለሥራ ቅርበት ሲሉ በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ የሚገኘውን ቤት መምረጣቸውን ይናገራሉ። የተወረሰው ቤታቸውም በድሮው ቀበሌ 58 የሚገኝ ሲሆን እስከዛሬም ድረስ የአዲስ አበባ ቤቶች አስተዳደር በባለቤትነት እያስተዳደረው እንደሚገኝ አመልክተዋል።

ቀበሌ 58 የነበረው ቤት ከመወረሱ በፊት የተመሩበት እና ቤቱን በአዋጁ መሠረት ለመንግሥት ያስረከቡት ሰነድ በእጃቸው እንደሚገኝ የተናገሩት ወይዘሮ እህተ ፍርሼ፣ ሰነዶቹንም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ማቅረብ ችለዋል።

### ከሰነዶች የተገኙ ማስረጃዎች

ከሰነዶች የተገኙ ማስረጃዎች በርካታ በመሆናቸው ሁሉንም ማቅረብ አይቻልም። ይሁንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ግራ ቀኙን አይቶ ይፈርድ ዘንድ ያስችሉታል ያልናቸውን ሰነዶች መርጠን በዚህ ጽሑፍ አካተናል።

**ሰነድ አንድ፡-** አቤቱታ አቅራቢዎቹ ቤቶች የመንግሥት ስለሆኑ የኪራይ ውል ተዋዋሉ ተብለው መነገሩን ተከትሎ አቤቱታ አቅራቢዎች ችግራቸው እንዲፈታ ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር አቤት ይላሉ። የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደርም ስለጉዳዩ ለማጣራት በቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ክ/ቤ/ል/ማኔ በቀን 07/01/2006 ለባለአደራ ቦርድ፣ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ ለአቃቂ ቃሊቲ መሬት ልማት ማኔጅመንት እና ለአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ደብዳቤ ጻፈ። ለሁሉም መስሪያ ቤቶች የተጻፈው ደብዳቤ በአንድ ቁጥር እና ቀን ነው። ይህን ተከትሎ የባለአደራ ቦርድ፣ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እና የአቃቂ ቃሊቲ መሬት ልማት ማኔጅመንት አቤቱታ ስለተነሳባቸው ቤቶች የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ሲገልጹ፤ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካም ለቤቶች ለተወሰኑ አመታት የመብራት እና የውሃ ወጪ ይችላቸው እንደነበር፤ ነገር ግን ስለቤቶች ምንነት እንደማያውቅ ለቤቶች አስተዳደር በደብዳቤ አሳወቀ።

ሁሉም መስሪያ ቤቶች ስለጉዳዩ እንደማያውቁ ይግለጹ እንጂ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ቤቶቹ የመንግሥት ናቸው ተብሎ ከመስሪያ ቤቶች እንደተገለጸ በማስመሰል ለአቤቱታ አቅራቢዎቹ ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጥ ቀረ።


**ሰነድ ሁለት፡-** አቤቱታ ከአቀረቡት መካከል ለተወሰኑት ሰዎች ካርታ ተሠርቶ የተሰጣቸው ሲሆን፤ ለተወሰኑት ደግሞ የአፈር ግብር እንዲከፍሉ በማድረግ ሰነድ አልባ መብት እንዲፈጠርላቸው የማድረግ እንቅስቃሴዎች አሉ።

**ሰነድ ሦስት፡-** የተወሰኑ አቤቱታ አቅራቢዎች በአዋጅ ቁጥር 47/67 ትርፍ ቤት እንደተወሰደባቸው፤ አሁን ያሉበትና በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ ሰፈር የሚገኘውን ቤት መርጠው እንደቀየሩ የሚያሳዩ ናቸው።

### በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የወረዳ 6 ዋና ሥራ አስፈጻሚ ምላሽ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ የምርመራ ክፍል በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣ የወረዳ 6 ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑትን አቶ ቶፊቅ ከድርን በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ ስለሚገኙ ቤቶች ምን ያውቃሉ? ሲል ጠይቆ ነበር። አቶ ቶፊቅም የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ቶፊቅ እንደገለጹት፣ ስለቤቶቹ የተወሰኑ ጉዳዮችን ቢያውቁም የተሟላ መረጃ ግን የላቸውም። ይሁን እንጂ፣ በእነዚህ ቤቶች የሚኖሩ ሰዎች ከወረዳው ማግኘት ያለባቸውን


ELICO
ኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ ኃ.የተ.የግ. ማህበር
ETHIO-LEATHER INDUSTRY Pvt.Ltd.Co.
UKAS QUALITY MANAGEMENT 026
5173/05

ቁጥር ኤሊኮ/2ሀ-35/06
Ref No.
ቀን 06/02/06
Date

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ለክ/ቤ/ል/ጽ/ቤት የቤቶች ልማት
ማኔጅመንት ዋና የሥራ ሂደት
አዲስ አበባ፣

ጉዳዩ፤ መረጃ ስለመስጠት፤

በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ አካባቢ ያሉ ቤቶች በተለምዶ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ቤቶች እንደሚባሉ ገልጻችሁ፤ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ መረጃ በመስጠት ትብብር እንድናደርግ በ22/01/06 በቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ክ/የቤልማኔ/068/06 በተጻፈ ደብዳቤ ጥያቄ ማቅረባችሁ ይታወሳል።

ምንም እንኳን በፋይል ውስጥ የተቀመጠ መረጃ ባይኖርም የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ወደ ግል ይዞታ ከመዛወሩ በፊት ቤቶቹ በፋብሪካው ባለቤቶች እንደተሠሩ የሚነገር ሲሆን ፋብሪካው በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት /ደርግ/ ሲወረስ ቤቶቹም የፋብሪካው ንብረት እንደነበሩ ተቆጥሮ የመብራትና የውሃ ፍጆታውን ፋብሪካው ሲከፍል ቆይቶ ፋብሪካው ለሚድሮክ ኢትዮጵያ ሲሸጥ የውሃና የመብራት ፍጆታው ከፍተኛ ሆኖ በመገኘቱ ክፍያው የተቋረጠ ሲሆን የነበረውን የመብራትና የውሃ አቅርቦት ጉዳይ በተመለከተ 11 ገጽ አባሪ አያይዘን አያቀረብን፤ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደርና የግንባታ ፈቃድ ባለሥልጣን … ካርታ ላይ ቤቶቹ በይዞታችን ሥር ያልተካተቱ መሆኑን …

ከሠላምታ ጋር

አገልግሎቶች እያገኙ አለመሆናቸውን ይገነዘባሉ። አሁን ላይ ነዋሪዎቹ ከወረዳው ማግኘት የነበረባቸውን እንደ ውሃ፣ መብራትም እና መሰል አገልግሎቶችን እያገኙ አይደለም። በዚህም ለከፋ ችግር ተዳርገዋል።

ከቤቶች ጋር ተያይዞ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ባለመኖሩ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ነዋሪዎች የተለያዩ አገልግሎቶችን ፈልገው ወደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ቢሮ በመጡ ጊዜ ከመንግሥት ማግኘት የሚገባቸውን የተለያዩ አገልግሎቶች ለመስጠት መቸገራቸውን አቶ ቶፊቅ ያስረዳሉ። አንዳንዴ ችግሩ በጣም የከፋ ሲሆን በሕግ የሚደገፍ ባይሆንም ነዋሪዎችን የንግድ ፈቃድ እንዲያመጡ በማድረግ አንዳንድ አገልግሎቶችን እየሰጡ እንደሚገኙም ነው የሚናገሩት። ነገር ግን ከመብራት እና ውሃ አገልግሎት ጋር ተያይዞ ሥራ አስፈጻሚው ላይ የሕግ ተጠያቂነት የሚያስከትል በመሆኑ እስካሁን ድረስ የተሟላ የመብራት እና ውሃ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረግ አለመቻላቸውን አመላክተዋል። ይሁንና እንደ ዜጋ ነዋሪዎቹ የመብራት እና የውሃን አገልግሎትን ማግኘት እንዳለባቸው ያምናሉ።

ስለጉዳዩ ብዙ የማውቀው ነገር የለኝም ማለት ግን ስለጉዳዩ እያጣራሁ አይደለም ማለት አይደለም ያሉት አቶ ቶፊቅ፤ የተፈጠረውን ውዝግብ በዘላቂነት ለመፍታት ችግሩን ከሥሩ እየመረመሩ መሆናቸውን አመላክተዋል።

በ2014 ዓ.ም ከበላይ አካል በተላለፈ ትዕዛዝ ነዋሪዎችን የኪራይ ውል አዋውሏቸው ተብለው ትዕዛዝ ተላልፎላቸው እንደነበር የሚናገሩት አቶ ቶፊቅ፣ ይሁንና ጉዳዩ ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት ማጣራት ስለሚጠይቅ ችግሩን በይደር ለመያዝ መገደዳቸውን ገልጸዋል።

በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ የሚገኙ ነዋሪዎች አሁን እየኖሩበት ባለው ቦታ ለረጅም ዓመታት ቆይተውበታል። በዚያ ቦታ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ትውልዶችን እንጂ መጀመሪያ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች አይገኙም። ስለሆነም ቦታቸው በሰነድ አልባ ታይቶ ወደ ሕጋዊነት መምጣት አለበት። በወረዳቸውም አሠራሩ እና መመሪያው በሚፈቅደው ልክ በርካታ ቤቶችን በሰነድ አልባ ሕጋዊ አድርገዋል። የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ነዋሪዎች ጉዳይም በሰነድ አልባ ወደ ሕጋዊ መስመር ቢገባ ለመንግሥት አሠራርም ሆነ ነዋሪዎቹ በሰላም ይኖሩ ዘንድ ምቹ መደላድል የሚፈጥር መሆኑን ያስረዳሉ።

እንደ እነዚህ ያሉ ቤቶች በሊዝ አዋጁም ሆነ ሰነድ አልባ በምንለው መንገድ ተላልፈውም ጭምር ሰነድ እንዲኖራቸው ቢደረግ እና ሰዎች እንዲጠቀሙበት መብት ቢፈጠር፤ እኔ እንደ ዜጋ ደስተኛ ነኝ። እንደ አንድ አመራርም የምደግፈው ጉዳይ ነው የሚሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፣ የክፍለ ከተማ ቤቶች ልማት ጽሕፈት ቤት ጽፎ በነበረው ደብዳቤ ተነስተን በደፈናው ቤቶችን ወደ መንግሥት ይግቡ ለማለት ሕጋዊ የሆነ የሕግ መሠረት ለመያዝ የሚያስቸግር መሆኑንም ተናግረዋል።

### በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ዳይሬክተር ምላሽ


በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የምርመራ ክፍል ስለአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ ቤቶች ምን ያውቃሉ? ተብለው የተጠየቁት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ዳኛው ገብረሚካኤል በበኩላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል።

የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሠራተኞች እና ቤቶቻቸውን በሚመለከት ቀደም ሲል ከነበሩ መረጃዎች እና ዶክሜንቶች መሠረት ተደርጎ ታሪካዊ አመጣጣቸው ቢገለጽ ስለቤቶቹ ምንነት የተሟላ እይታ እንዲኖረን ያደርጋል።

አሁን ላይ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ተብሎ የሚጠራው ድርጅት በ1948 ዓ.ም በአርመን ዜጎች የተመሠረተ ሲሆን፤ የመጀመሪያ ስሙም ዳር ማር ቆዳ ፋብሪካ ነበር። አርመኖች ፋብሪካውን ለመመስረት በማሰብ ፋብሪው የሚገኝበትን ቦታ በአካባቢው ይኖሩ ከነበሩ ባለእርስቶች ገዙ። ፋብሪካውንም ገነቡ።

በ1948 ዓ.ም ዳር ማር ቆዳ ፋብሪካ ተብሎ የተመሠረተው ድርጅት የደርግ መንግሥት መምጣቱን እና መወረሱን ተከትሎ በ1969 ዓ.ም የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ የሚል ስሜ ተሰጠው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ድርጅቱ ለሠራተኞቹ በማሰብ በፋብሪካው አካባቢ ከእንጨት እና ከጭቃ የተሠራ ፎቅ መሰል ጂ ፕላስ ዋን ቤት ሠርቶ በመኖሪያ ቤትነት እንዲገለገሉበት አደረገ።

# ፍረዱኝ




15/11/07ዓ.ም

# ማስታወቂያ

ለአዋሽ ቆዳ አከባቢ ለምትገኙ ነዋሪዎቻችን እንኳን ደስ አላችሁ!

በቀን 8/11/07ዓ.ም በቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ቤልማኔ/54/07ዓ.ም ከክፍለከተማ ኮ/ቤ/ል/ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ የአዋሽ ቆዳ አከባቡ የሠራተኞች መኖሪያ ቤቶች ከወረዳ 6 ኮ/ቤ/ል/ጽ/ቤት ጋር ቀርበው ውል እንዲዋዋሉ በላከው ደብዳቤ መሰረት በአቃ/ቃ/ክ/ከ/ወ/6/ኮ/ቤ/ል/ጽ/ቤት 2ኛ ፎቅ ቀርበው በቀጣይ 5 የስራ ቀን ማለትም 15/11/07 ዓ.ም-21/11/07 ዓ.ም ድረስ በመቅረብ እንድትዋዋሉ እናሳውቃለን ፡፡

ከሠላምታ ጋር



AKAKI KALITI SUB-CITY LAND
Land Development and management
Tenure Administration Transitional
Period Service coordination Project Office

ጉዳዩ፡- መረጃ ስለመስጠት ይመለከታል

ከሠላምታ ጋር



№ 584986

ቀንን ቀን ሲወልደው ለሠራተኞች መኖሪያ የተሠራው ቤት በእርጅና ምክንያት ፈራረሰ። የድርጅቱ ሠራተኞችም ለመኖር ይቸገሩ ጀመር። ይህን ተከትሎ ድርጅቱ ለሠራተኞች የሚሆን የጭቃ ቤት ለመሥራት በማሰብ ለበላይ መስሪያ ቤቱ ጥያቄ አቀረበ። በወቅቱ ለአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ የበላይ መስሪያ ቤት የነበረው ብሔራዊ ቆዳ እና ጫማ ድርጅት ነበር። የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ለብሔራዊ ቆዳ እና ጫማ ድርጅት የጭቃ ቤቶች ለሠራተኞች እንዲሠራላቸው ሲጠይቅ የዋጋ ግምቱንም ጭምር አስቀምጦ ነበር ጥያቄውን ያቀረበው። ጥያቄውም ተቀባይነት አግኝቶ ተፈቀደ። በዚህ መሠረት ለሠራተኞች በርካታ ቤቶች ተሠሩ። ሠራተኞችም እዚያው እየኖሩ ሥራቸውን ማከናወን ጀመሩ።

መጀመሪያ ላይ የጭቃ ቤት እንዲሠራላቸው ጠይቀው የነበሩት እና በብሔራዊ ቆዳ እና ጫማ ድርጅትም ቤት እንዲገነባላቸው ፍቃድ ያገኙት ሠራተኞች ቁጥር 48 እንደነበር አቶ ዳኛቸው ይናገራሉ።

ቤቶች ከተገነቡ በኋላ ቀጥሎ የመጣው የመብራት እና ውሃ ጥያቄ ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ ድርጅቱ ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣ መሬት አስተዳደር አመልክቶ መብራት እና ውሃ ገባላቸው። መብራቱ ሲገባ ሙሉ ወጪ በድርጅቱ የተሸፈነ ቢሆንም ከሠራተኞች የሦስት ወር ደመወዝ የሚቆረጥ ነበር። ይህ የሆነው አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ወደ ግል ተቋም ዞሮ ኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ በሚባልበት ወቅት ነው። በዚህ ጊዜ ነዋሪዎቹ በግላቸው የሚያስተዳድሩት መብራት እና ውሃ ተፈቀደላቸው። ይህ በእንዲህ እንዳለ የነዋሪዎቹ ቁጥርም ከ48 ወደ 59 አደገ። ቀጥሎም ወደ 61 ከፍ አለ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በ2002 ዓ.ም የቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በክፍለ ከተማው የቤቶች ቆጠራ አካሄደ። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ክፍለ ከተማው በራሱ ተነሳሽነት የቤቶች ቆጠራ ያካሂድ እንጂ የቤት ቆጠራው አገራዊ አልነበረም። ይህን ተከትሎ በወረዳ 6 ውስጥ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ የሚገኙ ቤቶች በነዋሪዎችም ሆነ በመንግሥት ያልተመዘገቡ ሆነው ተገኙ ።

ይህን ተከትሎ እነዚህ ቤቶች ምን ይሁኑ የሚል ጥያቄ ተነሳ። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች አስተዳደር ንዑስ የሥራ ሂደትም ለእነዚህ ቤቶች ለምን የኪራይ ተመን አይወጣላቸውም? ሲል በቀን 22/2/2003 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማን ጠየቀ።

በዚህም ምክንያት በጥቅምት ወር 2003 ዓ.ም በክፍለ ከተማ ደረጃ ኮሚቴ ተዋቅሮ፣ የከራይ ግምት ተዘጋጅቶ ለአዲስ አበባ ቤቶች አስተዳደር ተላከ። የተላከውን የኪራይ ግምትም ተከትሎ ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት በሚያዝያ 26 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የቤቶች የኪራይ ግምቱ መጽደቁ ተገለጸ። በዚህ መሠረት ቤቶቹ በኪራይ እንዲተዳደሩ የክፍለ ከተማው ቤቶች አስተዳደር ታዘዘ። በተያያዘም፣ ስለቤቶቹ የሚቀየር ነገር ካለ ወደፊት ሊቀየር እንደሚችል በደብዳቤው ተመላክቷል።

ይህን ተከትሎ «የቤቶች አስተዳደር የወሰነው ውሳኔ ትክክል አይደለም» ሲሉ 61 ሰዎች ለተለያዩ መስሪያ ቤቶች አቤቱታ አቀረቡ። አቤቱታ ከቀረበላቸው መስሪያ ቤቶች መካከልም የአዲስ አባበ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት፣ የኮንስትራክሽን እና ቤቶች ልማት ቢሮ፣ የወረዳ 6 ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የወረዳ 6 ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፤ እንዲሁም፣ የመሬት ልማት እና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ተጠቃሽ ናቸው።

አቤቱታ አቅራቢዎችም «ቤቱ ሲሠራ ቦታውን በስጦታ ከባለእርስቶች ወስደን በራሳችን የገንዘብ እና የጉልበት ወጪ ቤት ገንብተን እያለ፤ መብራት እና ውሃም በራሳችን ከፍለን አስገብተን እያለ መመሪያውን እና አሠራሩን ተከትሎ ቦታው ወደ ግል ይዞታ መቀየር አለበት እንጂ እንዴት በኪራይ እንዲተዳደር የኪራይ ተመን ይጣልበታል?» የሚል ጥያቄ ይዘው ነበር ሲከራከሩ የነበሩት።

ይሁን እንጂ የኪራይ ተመኑ በአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ጸድቆ ለወረዳ 6 ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ለወረዳ 6 ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፤ እንዲሁም፣ ለመሬት ልማት እና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ወደ ኪራይ እንዲገቡ የሚያዝዝ ደብዳቤ ተጽፎ ስለነበር ጉዳዩ አቤቱታ አቅራቢዎች በፈለጉት መልክ ሊፈታ አልቻለም። አቤቱታ አቅራቢዎቹ ችግራቸው ሳይፈታ በእንጥልጥል እስከዛሬ ድረስ ሊቆዩ ተገደዋል።

የአቤቱታ አቅራቢዎቹ ፍላጎት የመሬት ባለይዞታነት መብት እንዲፈጠርላቸው ሲሆን፣ የወረዳው እና የክፍለ ከተማው ቤቶች ፍላጎት ግን የወጣውን የኪራይ ተመን መሠረት አድርጎ ለማከራየት ነበር። ይሁንና የአቤቱታ አቅራቢዎቹ ጥያቄ የመሬት ባለይዞታነት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው የሚጠይቅ በመሆኑ የቤቶች አስተዳደር መሬት መስጠት እንደማይችል ገልጾ፤ የመሬት ባለይዞታነት ጥያቄአቸው ተፈጻሚነት እንዲኖረው ከፈለጉ ጉዳዩን ለቤቶች አስተዳደር ሳይሆን ለመሬት አስተዳደር ማቅረብ እንደሚገባቸው ምክረ ሀሳብ እንደሰጧቸው ተናግረዋል።

ዛሬም ቢሆን የመሬት ባለይዞታነት ጥያቄ የሚመለሰው በመሬት አስተዳደር እንጂ በቤቶች ልማት ጽሕፈት ቤት አለመሆኑን የገለጹት አቶ ዳኛቸው፤ የሰዎች ጥያቄ ምላሽ ያገኝ ዘንድ የቤቶች አስተዳደር የራሱን ሚና እንደሚጫወት ገልጸዋል። በቅርቡም የቤቶች አስተዳደር የሚደርስበትን ቁርጥ ያለ ውሳኔ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚያሳውቁ ገልጸዋል።

የቤቶች አስተዳደር ከመሬት ተነስቶ የቤት ኪራይ ግምት ይሰጣል ወይ? ይህንን አሠራርስ ሕጋዊ የሚያደርግ መመሪያ ወይም አሠራር አለ ወይ? ተብለው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የተጠየቁት አቶ ዳኛቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

የተለያዩ መመሪያዎች በየጊዜው እየተሻሻሉ መጥተዋል። እኔ የማውቃቸው መመሪያዎች አንደኛው መመሪያ ቁጥር 4፣ 2009 ሲሆን፤ መመሪያ ቁጥር 5፣ 2011 ሁለተኛው፤ አሁን በቅርቡ የወጣው መመሪያ ቁጥር 6፤ 2015 ደግሞ ሦስተኛው ነው። በተዋረድ እነኝህ መመሪያዎች በየዕለቱ እየተለወጡ የመጡበት ሁኔታ አለ። ግን በአጋጣሚ ሆኖ እነኝህ ሁሉም መመሪያዎች ከኪራይ ተመን አወጣጥ እና ከቤት ቁጥር አሰጣጥ አኳያ ሲታይ በማንኛውም መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም በግለሰብ የተሠሩ ቤቶች ወደ መንግሥት አስተዳደር ይግቡ ተብሎ ከታች፣ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክፍለ ከተማው በአስተዳደሩ ሲወሰን እና ወደ መንግሥት ቤትነት ሲቀየሩ የቤት ቁጥር የመስጠት፤ የኪራይ ተመን የማውጣት የቤቶች አስተዳደር ሥራ ይሆናል። ነገር ግን፣ በማንኛውም ሁኔታ የቤቶች አስተዳደር ከመሬት ተነስቶ የኪራይ ተመን ማውጣት አይችልም። እዚህ ላይ የአስተዳደሩ ውሳኔ የሚለውን በአጽኖት ማየት ይገባል። ነገር ግን፣ በማንኛውም ሁኔታ የበላይ መስሪያ ቤትም ቢሆን የቤቶችን ተመን አውጥቶ ወደ ኪራይ አስገቡት የማለት ሥልጣን የለውም።

ለምሳሌ አንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ ለአንድ ለተወሰነ ፕሮጀክት፣ በአንድ አካባቢ ቤት ቢሠራ እና ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ቤቶቹን ለመንግሥት አስረክቦ ሊሄድ ይችላል። ለመንግሥት አስረክቦ ሲሄድ በመንግሥት በኩል የተረከበው አካል ለሕዝብ አገልግሎት እንዲውል ሲታሰብ የኪራይ ተመን ይወጣለታል።

አቤቱታ ካቀረቡት ሰዎች መካከል ለተወሰኑ ሰዎች ተለይቶ ካርታ ተሰጥቷቸዋል፤ ግማሾቹ ደግሞ የአፈር ግብር እየከፈሉ ይገኛሉ። ስለዚህ ምን ትላላችሁ ብለን የጠየቅናቸው አቶ ዳኛቸው ይህን ጉዳይ ለመሬት ማኔጅመንት እንዳቀረቡትና መሬት ማኔጅመንት ደግሞ ምንም ዓይነት ካርታ እንዳልሰጠ በደብዳቤ እንደተገለጸላቸው ተናግረዋል።

የእናንተ መስሪያ ቤት ስለቤቶቹ ለማጣራት ለባለ አደራ ቦርድ እና ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ደብዳቤ ጽፎ ነበር። ለደብዳቤአችሁ ምላሽ የሰጡት ከላይ የተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች ስለቤቶቹ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ገልጸዋል። ታዲያ እናንተ ከእነሱ መረጃ ካላገኛችሁ ቤቶችን የእኛ ናቸው ማለት ትችላላችሁ ወይ? ስንል አቶ ዳኛቸውን ጠይቀን ነበር። ከላይ የተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች ውዝግብ የተነሳባቸውን ቤቶች የቤቶች አስተዳደር መሆናቸውን ከገለጹ ውዝግብ የተነሳባቸው የቤቶች አስተዳደር ናቸው ሊባሉ እንደማይችሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

አሁንም ቢሆን ከቤቶች ጋር ተያይዞ የተፈጠረው ችግር ሊፈታ የሚችለው በክፍለ ከተማው የመሬት አስተዳደር ነው ያሉት አቶ ዳኛቸው፤ ችግሩ መፍትሄ እስከሚገኝለት ድረስ መመሪያ እና አሠራርን ተከትለው ተባባሪ እንደሚሆኑ ገልጸዋል።

## የጋዜጠኛው ትዝብት

ለቤቶቹ የኪራይ ተመን እንዲወጣ የተደረገው የ2002 ምርጫን ተከትሎ ነው። በዚህ ምርጫ አቤቱታ ከተነሳባቸው ቤቶች በአንዱ ይኖሩ የነበሩት አቶ አስራት አራርሳ የተባሉ ግለሰብ የምርጫ ታዛቢ ሆነው ይመረጣሉ። ይሁንና ምርጫው ተጠናቆ በምርጫ ሰነዱ ላይ ፊርማቸውን እንዲፈርሙ ሲጠየቁ ምርጫው ሕጋዊ ሂደቱን ስላልጠበቀ አልፈርምም ይላሉ። ይህን ተከትሎ በወረዳ ስድስት ይሠሩ የነበሩ አቶ ገብረሚካኤል የተባሉ ግለሰብ አንተ እኮ መጀመሪያውኑ የአነግ ተላላኪ እንደሆንክ እናውቅ ነበር። ፊርማውን አልፈርምም ማለትህ የምትኖርበትን ቤት እንደሚያሳጣህ እንዳትረሳ ብሎ ይዝታል። ይህን ተከትሎ ዛቻው ውሎ ሳያድር ተግባራዊ ሆነ። አንድን ሰው ለመበቀል የተወረወረ ጦር 65 አባወራዎችን ወጋ። ይህ ከበርካታ ሰዎች ጠይቀን ያገኘነው መረጃ ነው።

ሌላውና ጋዜጠኛው መታዘብ የቻለው ደግሞ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ድርጅት እራሱ ሕጋዊ ካርታ ያገኘው በ2006 ዓ.ም መሆኑን ነው። ድርጅቱ ከ2006 ዓ.ም በፊት ካርታ አልነበረውም። ይህ ሰነድ በማስረጃነት ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ቀርቧል። ሌላው ከድርጅቱ ጋር ተያይዞ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ሦስት ቤቶች መወረሳቸውን እና በአሁኑ ወቅት ከእነኝህ ሦስት ቤቶች አንዱ ተዘግቶ የሚገኝ ሲሆን፣ ቀሪዎቹን ሁለት ቤቶች ግን የአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት እና ቻይናውያን በመኖሪያነት እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ተመልክተናል።

የመጨረሻው ትዝብት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ዳይሬክተር እና በወረዳ 6 ዋና ሥራ አስፈጻሚ የተሰጠው ምላሽ ቤቶችን ለአቤቱታ አቅራቢዎች ለመመለስ አንድ እርምጃ ወደ ፊት የተጓዘ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ዳይሬክተር የሆኑትን አቶ ዳኛቸው ገብረሚካኤልን እና በወረዳ 6 ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑትን አቶ ቶፊቅ ከድር አለማመስገን ንፉግነት ነው።

በቀጣይ በሚኖረን ዝግጅት የነዋሪዎችን አስተያየት እና አጠቃላይ ጉዳዩ የት ደረሰ የሚለውን የመጨረሻ ክፍል ይዘን እንቀርባለን።

**እስከዚያው ቸር እንሰንብት!!**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## «ምሥጢረ አፈር» - በሀገረ ኢትዮጵያ

### የመነሻ ሃሳብ፤

በዚሁ አንጋፋ ጋዜጣ የመጋቢት 17 ቀን 2015 ዓ.ም እትም ላይ አንድ ዜና ወደ አንባቢያን ደርሶ ነበር። የዜናው ርእስ፤ "በኢትዮጵያ ለእርሻ ከሚውለው መሬት ሰባ ሚሊዮን ሄክታሩ አሲዳማ ነው" የሚል ነበር። በዜናው ዝርዝር ሃሳብ ውስጥ "አራት ሚሊዮን ሄክታር አሲዳማ መሬት ምርት ለማምረት የማይቻልበት ደረጃ ላይ መድረሱ" በሚገባ ተሰምሮበታል።

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የአፈር ሀብት ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አማካይነት የተገለጸው ይሄ ሀገራዊ እውነታ ለሙያው ቅርበት ባላቸው፣ በአስፈጻሚና በፈጻሚ ተቋማት ባለሙያዎች ዘንድ ብቻ ሳይሆን ከአፈር ጋር ተቆራኝቶ ለሚያኖረን ባለውለታ ለአርሶ አደሩና ለመላው የሀገሪቱ ዜጎች ጭምር ጉዳዩ በእጅጉ ማሳሰቡ የሚቀር አይደለም። ሚሊዮን ርሃብተኞች በሚገኙባት ሀገር በሚሊዮን የሚቆጠር ሄክታር መሬት ታማሚና መካን ሲሆን ያሳስባል፤ ያስጨንቃልም።

ይበልጥ በሥጋት የልባችንን ትርታ እንዲጨምር ከሚያደርጉት የሥራ ኃላፊው ገለጻዎች መካከል የሚከተሉት መደምደሚያዎች በእጅጉ በሀገራዊ ተስፋ ችን ላይ ጥላቸውን አከብደውብናል። አንደኛ፡- ኢትዮጵያ ማግኘት ካለባት ምርት ግማሹን እያጣች ነው። መሬቱ ቢታከም ኖሮ ሀገሪቱ አሁን ከምታመርተው ምርት ከሃምሳ እስከ መቶ በመቶ እጥፍ ምርት ማምረት ትችላለች።

" ሁለት፡- "በአሲዳማነት ከተጠቃው አፈር ሕክምና የተሰጠው ሦስት በመቶ ብቻ ነው።" ሦስት፡- "አንድ ሄክታር አሲዳማ መሬት ለማከም በትንሹ 30 ኩንታል ኖራ ያስፈልጋል። ይህ 30 ኩንታል ኖራ በግዥ ይቀረብ ቢባል እንኳን ከ30 ሺህ ብር በላይ ይጠይቃል። ሰፋ ተደርጎ አሲዳማ መሬቱን አክሞ ጤንነቱን ለመመለስ በጠቅላላው እስከ 45 ቢሊዮን ብር በጀት ይጠይቃል።" ኃላፊው በዝርዝር የገለጹልን ሪፖርት ነው።

በመሠረቱ ኢኮኖሚዋን በግብርና ዘርፍ ላይ አንተርሳ ለምትኖረውና ህልውናዋ ከአፈር ጋር ለተቆራኘው ሀገራችን ይህ ዜና አሳሳቢ ተብሎ ብቻ የሚገለጽ ሳይሆን በዘርፉ ባለሙያዎች፣ በባለጉዳዩ ሚኒስቴር መ/ቤትና በመላው ዜጎች ዘንድ "የመፍትሔ ያለህ" እየተባለ የሚጮኽበት ዋና ሀገራዊ አጀንዳ ሊሆን በተገባ ነበር።

ይህንን ዜና ያነበቡና ከተለያየ የመረጃ ምንጮች ያዳመጡ የዘርፉ ባለሙያዎች ወይንም ቀደም ብለው "ምሥጢሩን" እያወቁ ዝምታን በመምረጥ "ዝም አይነቅዝም" የሚል የ"ዳተኛነት" መርህ የሚከተሉ ቀዳሚ ተጠያቂዎች ስለምን ተረጋግተው ሊቀመጡ እንደቻሉ የመጠየቅ መብት ያለው አስፈጻሚውና በተለይም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ እስካሁን ስለምን "ጆሮ ዳባ ልበስ" እንዳለ በካርዳችን ለሥልጣን ወንበር ያበቃናቸውን አባላቱን አምርረን እንሞግታቸዋለን። ከእነርሱ በላይ ከፍ ያለ አካል ካለም "ይግባኝ!" ብለን አቤቱታችንን እናቀርባለን።

ሀገሪቱ ልታመርት የምትችለውን ሃምሳ ከመቶ በረከት ያሳጣንን ይህንን "የተፈጥሮ መርገምት" ስለምን ኢትዮጵያ እንኮኮ ብላ ተሸክማ እንደኖረች ችግሩ ተፍረጥርጦ ሊገለጽልን ይገባል። ምናልባት በተጫነን ሀገራዊ "አዚም" ተሸንፈን የችግሩ ክብደት አልተሰማን ከሆነም ብንመክርበት አይከፋም። በብዙ ሀገራዊ ችግሮቻችን ምክንያት "ድባቴ" ውስጥ ወድቀን የማሸለባችን ውጤት ከሆነም "አእምሯችን ውስጥ ያለውን የተስፋ መቁረጥ ብጉንጅ አፍርጠን" ልንፈወስ ይገባል።

"ሀገራዊ ድባቴያችን" ወሰኑ ይህ ልኩ የሚባል ብቻ ሳይሆን ከእኛ የሚፎካከር ሀገር ስለመኖሩም እርግጠኞች አይደለንም። የኑሮ ውድነቱ ከደመና በላይ ከፍ ብሎ ቁልቁል ተጭኖ "እህህ" እያልን ነው። የፖለቲካው ጡዘት ናላችንን አዙሮ ሲያጥወለውለን "የባሰ አታምጣ" ከማለት ውጭ ምንም አልፈየድንም። ማህበራዊ መስተጋብራችን ውሉ ጠፍቶበት ሲጎለጎል እያስተዋልን "ክፉ ቀንና ቅዝምዝም የሚታለፈው ጎንበስ ተብሎ ነው" በሚለው ፈሊጥ ራሳችንን አስከነናል። በኤሎሄ ጩኸት ወደ ጸባኦት እየቃተትንም "ነገም ሌላ ቀን ነው" በማለት በተስፋ በመኮራመት ከጣሪያችን በታች ተሰባስብን ቀንን እንገፋ ካልሆነ በስተቀር እየተወራጨን አልተንፈራገጥንም።

ስለዚህ፡- አፈራችን ለበደነበት የአሲዳምነት አደጋም "ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ በለው" እንዳለው መከራኛ ዜጋ በድባቴ ውስጥ ብንሆን ላይፈረድብን ይችል ይሆናል። ምናልባትም ያንን ዜና እንደ ወትሮ የእለት ክስተት ቆጥረን ማለፋችን ስለዚሁ ይሆን ወይ ብለን ብንጠይቅ ፖለቲካውንና ፖለቲከኞችን የምናስከፋ አይመስለንም። ለማንኛውም መነሻ ሃሳባችንን በዚህ የማጠቃለያ ሃሳብ "በልጥ አስረነው" (ትኩረት ቢሰጠውም ባይሰጠውም ለማለት ነው) "የምሥጢረ አፈርን" ነገረ ጉዳይ ከግብርናና ከኢኮኖሚ ጉዳይ ነጠል አድርገን ሌሎች "አፈር ጠቀስ" ጉዳዮችን በማስታወስ የጠነነውን ርእሰ ጉዳይ ለማለዘብ እንሞክራለን።

### «አፈር እንደ ዋዛ»

ይህ ንዑስ ርእስ ይህንን ጸሐፊ ለአንድ ሀገር አቀፍ ሽልማት አብቅቶት እንደነበር ለኩራት ሳይሆን ለትዝታ ያህል ማስታወሱ ቦታው እንደሆነ ያምናል። በ1978 ዓ.ም የባህል ሚኒስቴር አዘጋጅቶ በነበረው ሀገር አቀፍ የሥነ ጽሑፍ ውድድር በአጭር ልቦለድ ዘርፍ ያሸነፈው ይህ አምደኛ ተወዳድሮ የሁለተኛ ደረጃ ማእረግ ያገኘበት "አፈር እንደ ዋዛ" በሚል ርእስ ያዘጋጀው ጽሑፍ ነበር። የርእሱ ውስጥ ከራስ ወደ ራስ መሆኑን ልብ ይሏል።

ከዚያ አሸናፊ ጽሑፍ መካከል ጥቂት ኃይለ ቃላትን እንዘክር። "ከሕጻንነቴ ጀምሮ እየተከተለ ያቃጭል የነበረው የአፈር አደራ በጉልምስና እድሜዬም መደውሉን አልተወም። ዋ! ለካንስ አፈራችን ኢትዮጵያችን ናት። ድንበሯን የጀግኖች አጥር ያጠረው። እናም ህልውናችን፣ አርማችን፣ ኩራታችን፣ እስትንፋሳችን፣ የብልጽግና መገኛ ሀብታችን (ብልጽግና የተጠቀሰው በዛሬ ይዘቱ እንዳልሆነ ልብ ይሏል - ሆይ ጉድ ቃላትም ያስፈሩን ጀመር!?)፣ ሀብታችን፣ የአጽማችን ማረፊያ ርስታችን፣ ውርሳችን፣ ይህ እንደ ዋዛ የምንናየው አፈራችን ለካስ እኛነታችን ነውና? ሳላውቀው ሳናውቀው! አፈር ቴክኖሎጂና ሳይንስ፣ አፈር ግብርና፣ አፈር ዳር ድንበር፣ አፈር፣ አ.ፈ.ር፣ አ-ፈ-ር..." "ስሞተኛውና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች፤ ዳግላስ ጴጥሮስ፤ ገጽ 38 - 51።)

### «ምሥጢረ አፈር»

አፈር በርግጥም ምሥጢር ነው፤ ጥበብም ነው። ለዓለማችን ተመራማሪዎች ዕንቆቅልሽ ሆነው ከኖሩት "ድፍን ዕንቅላል" ከሚባሉ ርእሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ አፈር ነክ ምሥጢር መሆኑም እርግጥ ነው። የዘርፉ ሳይንቲስቶች የምርምር ውጤት የሆነው ማረጋገጫ በራሳቸው ቋንቋ እንደሚከተለው ይነበባል።

"One teaspoon of topsoil contains around one billion individual microscopic cells and around 10,000 different species" ይገርማል። በአንድ የሻሂ ማንኪያ የሚዘገን አፈር በቢሊዮን የሚቆጠሩ "ፍጥረቶችን" አቅፎ ይዟል። የጥናት ውጤቱ ማጠቃለያም በተነጻጻሪነት እንዲህ ተድምድሟል። "One teaspoon of soil contains more living organisms than there are people in the world" (Capital coalition, August 31/2017)። እውነታው ይህ ብቻ አይደለም፤ ሦስት ሴንቲ ሜትር (አንዳንዶች አንድ ሴንቲ ሜትር ይላሉ) አፈር ለመፍጠር/ለመፈጠር (generating ይሉታል)1000 ዓመታትን እንደሚፈጅ ሳይንቲስቶች ግምታቸውን ሰጥተዋል።

አፈር እስከዚህ የከበረና ምሥጢር የተሸከመ የፈጣሪ ችሮታና ስጦታ ብቻ ሳይሆን ሌላም የገዘፈ ትርጉም አለው። እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጅ ራሱ የተፈጠረው ከአፈር ነው። በፍጻሜውም ወደ አፈር መመለሱ እውነት ነው። ይህንን ማረጋገጫ ከሚሰጡን የቅዱሳት መጻሕፍት መካከል ጥቂት ጥቅሶችን እናስታውስ። "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለን ‹አለው›" (ዘፍጥረት 2፡7፤ 3፡19)።

በቅዱስ ቁርዓን ውስጥም በተመሳሳይ ይዘት ተገልጧል። "አላህ ሰውን ከአፈር ፈጠረው። ከዚያም ለርሱ (ሰው) "ኹን" አለው፤ ኾነም (ሱረቱ አል-ኢምራን 2፡59። ያ ሁሉንም ነገር አሳምሮ የፈጠረው፤ የሰውንም ልጅ አፈጣጠር ሂደት ከጭቃ የወጠነ (አምላክ) ነው። (ሱረቱ አል-ሰጃዳ 32፡7)"

አፈር የዚህን ያህል የላቀ ክብር ካለውና የሰው ልጆችም የተፈጠርነውና የተሸከምነው ገላ በአፈር የተለበጠ ማንነት ከሆነ ዘንድ ስለምን በሚሊዮን ሄክታር የሚቆጠረው የኢትዮጵያ የአፈር ፀጋ በአሲዳምነት ተፈርጆ ዘር እንዲያመክን ፈረድንበት? ስለምንስ ፈጣሪ በቸርነቱ ያደለንን አይተኬ ስጦታ አጣጥለን እንዳልባሌ ጉዳይ በቸልታና በግዴለሽነት እንክብካቤ ነፈግነው።

የመከነ አፈር የተለየ ክብካቤ ተደርጎበትና ታክሞ በቀጣይነትም በጎርፍ ከመሸርሸር ቢጠበቅና በእጽዋት ቢሸፈን መልሶ የማገገም ተስፋ እንዳለው የዘርፉ ተመራማሪዎች ያረጋግጣሉ። አፈራችን በተጠቀሰው ከፍተኛ ጉዳት ተጠቅቶ በአሲዳምነት ቢፈረጅም፤ ኢትዮጵያ በየክረምቱ በተከለቻቸውና ወደፊትም በምትተክላቸው በሚሊዮን በሚቆጠሩ የእጽዋት ችግኞችና ሰፋፊ የእርከን ሥራዎች ልትመሰገን ይገባል። ይህ ሀገራዊ ተፈጥሮን የመታደግ ርብርብ እየተሄደበት ባለው ፍጥነት የሚቀጥል ከሆነ የመከነው አፈራችን ተፈውሶ የበረከት ምንጭ እንደሚሆን ለማመን አይቸግርም።

### ከአፈር ተፈጥሮ አፈር የተሸከመው ማንነታችን ሲፈተሽ፤

የሰው ዘር በሙሉ የተፈጠረው ከአፈር እንደሆነና የፍጥረት ሩጫውን ሲፈጽምም ወደ ወጣበት አፈር እንደሚመለስ በቅዱሳን መጻሕፍት እማኝነት ማረጋገጣችን ከላይ በዝርዝር ቀርቧል። ይህንን እውነታ መነሻ በማድረግም ማንነታችንን መፈተሹ ማስተዋል ስለሆነ በጥቂት ወሳኝ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ከራሳችን ጋር እንድንነጋገር ጸሐፊው ዳግላስ "እባካችሁ ሞክሩት" ብሎ ይማጸናል።

እያንዳንዳችን የተሸከምነው አፈር ለም ነው ወይንስ ዘር አምካኝ አሲዳም አፈር? ከተሸከምነው የአፈር ቁልል ውስጥ ምን ያህል መቶኛው ለሌሎች መልካም ፍሬ አፍርቶ ስንቶቹን ታደገ? በተለየ ምልከታ እድልና ጊዜ ተገጣጥሞላቸው የሕዝብ አገልጋይ የሆኑ ሹመኞች ምን ያህል ከአሲዳምነት ባህርይ ራሳቸውን ጠብቀዋል። ዘር ዘርተው ለዛሬውና ለነገው ትውልድ ፍሬ እንዲያፈሩበት በአደራ የተቀበሉት ሥልጣናቸውስ ምን ያህል ለምርታማነት አብቅቷቸዋል።

በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ገበሬና ዘር የሰጠው ድንቅ አስተማሪ ምሳሌያዊ ታሪክ (Parable) እዚህ ቦታ ቢጠቀስ ቦታው ይመስለናል። "እነሆ አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ። ሲዘራም ሳለ አንዳንዱ ዘር መንገድ ዳር ወደቀ፣ ተረገጠም፣ የሰማይ ወፎችም በሉት። ሌላውም በጭንጫ መሬት ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፤ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። ወፎችም መጥተው ለቅመው በሉት።

አንዳንዱ ዘር አፈሩ ስስ በሆነ ድንጋያማ መሬት ላይ ወደቀ፤ አፈሩ ስስ ስለሆነም ፈጥኖ በቀለ። ነገር ግን ፀሐይ ሲመታው ጠወለገ፤ ሥር ባለመስደዱም ደረቀ። አንዳንዱም ዘር በእሾህ መካከል ወደቀ፣ እሾሁም አደገና ቡቃያውን አንቆ አስቀረው። ሌላው ዘር ደግሞ በጥሩ ለም መሬት ላይ ወደቀ፤ ፍሬም አፈራ፤ አንዱ መቶ፣ አንዱ ስልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ። ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!" (የማቴዎስ ወንጌል 13፡3 - 9)።

የዚህ ጽሑፍ ማጠቃለያም ይኸው ሃሳብ ነው። ቁጥራቸው ያነሰ ቢሆንም አንዳንድ ባለስልጣናት የተሸከሙት የሥልጣን ዘር በመልካም መሬት ላይ ስለተዘራ ቀን ከሌት ሕዝቡን በትጋት እያገለገሉ መልካም ፍሬ ሲያፈሩ እየተመለከትን ነው። ለእነዚህ ሹመኞች ያለን የምሥጋና ቃልና ማበረታቻ ነው። ተግተው በሥልጣን ወሰናቸው ዙሪያ በርካታ የተንዠረገጉ ፍሬዎችን እንዲያፈሩም ምኞታችን ነው።

አንዳንዶችም አሉ፡- በሾሃማው ልባቸው ላይ የሥልጣን ዘር ተዘርቶ ሕዝብን ሲያስለቅሱ ውለው የሚያድሩ። ለእነዚህ መሰሉ ሹመኞች ልብ ይስጣቸው ከማለት ውጭ ምንም ማለት አይቻልም። ሕዝቡን በጉቦና በመማለጃ፣ በሴራና በተንኮል በማስመረር የሥልጣን ዘመናቸውን በመፈጸም የተመኩበት ካባቸው ወልቆ ተራ ሰው የሆኑ እለት ማሕበረሰቡን የገረፉበት ጅራፍ እነርሱ ጀርባ ላይ እንደሚያርፍ ቢጠረጥሩ አይከፋም።

በአንዳንድ ድንጋይ ልብ ሹመኞች ላይ የተዘራው የሥልጣን ዘርም ያለ ውጤት "እከሌ" አሰኝቶ ከማስጠራቱ በዘለለ ፍሬ የማያፈሩ "ውሎ ገብ" የሚባሉ ዓይነቶች ናቸው። በተለይም የፖለቲካ ካድሬ የተሰኙት ቁጥራቸው የበዛ ነው። እነዚህ ሕዝብ በአግባቡ ከማስተዳደር ይልቅ በጭንጫና ደንዳና ልባቸው ሕዝብን የደም እምባ በማስነባት ውለው የሚገቡ ችግር ፈጣሪዎች "እርሶ ያሰኛቸው" ጀንበር ሲጠልቅና ተራ ሰው ሲሆኑ ከማሕበረሰቡ የሚገጥማቸውን አደጋ ከወዲሁ ገምተው ድንጋዩን ልባቸውን ወደ ሥጋ ልብነት ቢለውጡ ይበጃቸው ይመስለናል።

ለሕዝብ ኖረው ለሕዝብ እስከ መሞት የጨከኑና መንግሥታዊ ሥልጣናቸው በለም ልባቸውና መንፈሳቸው ላይ የተዘራባቸውን ትጉሆችና ታታሪዎችን ደግመን እናመሰግን። እነዚህ ሹመታቸው እንደ ሺህ ሞት የሚያስፈራቸው የሕዝብ ልጆች ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም በፍሬያቸው እየመዘንናቸውና በየሥራ መስካችንና በየጓዳችን እያደነቅናቸው ስንባርካቸው መዋላችን አልቀረም።

በመቶ፣ በስልሳ፣ በሰላሳ እጥፍ የሚቆጠረው ፍሬያቸውም በራሱ መዓዛው ከሩቅ መጣራቱ አልቀረም። ለኢትዮጵያ የምንመኘው እንደነዚህ ዓይነቶቹን ለሕዝብ የተሰጡ "የወርቃማ" ፍሬ ባለጸጎችን ነው። እንደነዚህ አይነት ባለሥልጣናት ከበዙልን "አሲዳም አፈር የተሸከሙቱ" እየከሰሙ ስለሚሄዱ ተስፋችን ይለመልማል። "ጆሮ ያለው ይስማ!" አዋጅን ደግመን በማወጅ ለሕዝባችን ሰላምን ለዜጎችም በጎ ፈቃድን እንመኛለን። የመከነው ሀገራዊ አፈራችንም ሆነ የተሸከምነው የማንነታችን ቁልል አፈር ሁለቱም ለፍሬ ይብቁልን። ሰላም!

# አበረታች ውጤት እያስመዘገበ ያለው የአበባ የውጭ ንግድ

**ፍሬሕይወት አወቀ**




ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ዘርፍ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የዕጸ ጣዕም ምርቶችን ማምረት የሚያስችል ምቹ የአየር ሁኔታና እምቅ የተፈጥሮ ሃብት እንዳላት ይታወቃል።ይህ እምቅ ሀብት ለአገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ተስፋ ተጥሎበት በሆርቲካልቸር ዘርፍ ላይ እየተሰራም ይገኛል።ዘርፉ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት በኩል ተጠቃሽ መሆን የቻለም ሲሆን፣ ከግብርና ምርቶች ከቡና በመቀጠል ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እያስገኘ ያለም ነው።

አገሪቷ ለዘርፉ ካላት ተፈጥሯዊ ሃብት በተጨማሪ የሆርቲካልቸር ዘርፍ አነስተኛ በሆነ ቦታ መልማት የሚችልና ሰፊ የእርሻ ቦታን የማይጠይቅ መሆኑ ደግሞ ዘርፉን ይበልጥ ውጤታማ እንዳደረገው መረጃዎች ያመለክታሉ።ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ዘርፍ አበባ አምርታ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ከጀመረች ከሁለት አስርት ዓመታት ያልበለጠ ዕድሜ ብቻ ያላት ብትሆንም፣ ባላት ዕምቅ ሃብት የተነሳ አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡

አገሪቷ ያላትን ዕምቅ የተፈጥሮ ሃብት በመጠቀም ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንድትችል መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት የድርሻቸውን እየተወጡ ይገኛሉ።የሆርቲካልቸር ዘርፍ በዋናነት ኤክስፖርት ላይ ያተኮረ በመሆኑ የገበያ መዳረሻ የሆኑ አገራት በሚፈልጉት የጥራት ደረጃ ምርቱ ተመርቶና ተዘጋጅቶ እንዲላክ ይሠራል።

ምርቱ በአብዛኛው ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ነው፤ አብዛኞቹ አምራቾችም የውጭ አገር ባለሃብቶች ናቸው። በመሆኑም አምራችና ገዥ አገራትን በማገናኘት የገበያ ትስስር መፍጠር እንዲቻል የኢትዮጵያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማህበር የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ ቆይተዋል።

ማህበሩ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከልም የተለያዩ ኤክስፖዎችን ማዘጋጀት አንዱ ነው።ማህበሩ በሚያዘጋጃቸው ኤክስፖዎች አማካኝነትም አገሪቷ ለኢንቨስትመንት ምቹ እንደሆነች ከማስተዋወቅ ባለፈ ሰፊ የገበያ ትስስር መፍጠር ያስችላል።በቅርቡም የሆርቲካልቸር ዓለም አቀፍ ኤክስፖ ለስምንተኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ በሚሊኒየም አዳራሽ ተዘጋጅቶ እንደነበር ይታወሳል።ኤክስፖው ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ዘርፍ ያላትን እምቅ አቅም በማስተዋወቅና ዓለም አቀፍ የገበያ ትስስርን በመፍጠር፣ የአቅርቦት ሰንሰለትን በማሳደግ እንዲሁም የተወዳዳሪነት አቅምን በማጎልበት ረገድ ትልቅ ፋይዳ እንደነበረው የኤክስፖው ተሳታፊዎች ይናገራሉ፡፡

ወጣት ጃለኔ አበበ የማርጅን አበባ ልማት የኢንቫይሮመንት ባለሙያ ናት።እሷ እንደምትለው፤ ማርጅን የአበባ ልማት የሆላንድ ዜግነት ባላቸው የውጭ ባለሃብት የተመሰረተ ሲሆን፤ ድርጅቱ በኬንያም ሰባት የአበባ እርሻ ቦታዎች አለው። ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ሶስት የአበባ እርሻ ቦታዎች አሉት።

ማርጅን የሚያመርታቸው አበቦች ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ ገበያ የሚላኩ በመሆናቸው በውጭ ምንዛሬ ዕድገት ላይ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።ወጣት ጃለኔ የገበያ መዳረሻቸውን በተመለከተ በዋናነት ሆላንድ ላይ ተደራሽ የሚያደርጉ መሆናቸውን ጠቅሳ፣ በበርካታ የአውሮፓ አገራት ላይም ተደራሽ እንደሆኑና ማርጅን አበባ በዓለም ገበያው እጅጉን ተፈላጊ እንደሆነ ነው ያስረዳችው።የማምረት አቅማቸውን በተመለከተም በዓመት ከ30 ሚሊዮን በላይ የአበባ ግንድ (ስቲም) ወደ ውጭ ገበያ እንደሚላክም ወጣት ጃለኔ አመላክታለች።

የሬድፎክስ ኢትዮጵያ አበባ ልማት ሲኒየር ኳሊቲ አሹራንስ ማናጀር አቶ ሞሲሳ ተፈሪ እንዳሉት፤ ሬድፎክስ ኢትዮጵያ ፔንሴቲያ እና ፔላርጎን የተባሉ ሁለት የአበባ ዝርያዎችን እያመረተ ለውጭ ገበያ ያቀርባል።ወደ ውጭ ገበያ የሚቀርቡት እነዚህ የአበባ ዝርያዎችም አራት ሴንቲሜትር ቁመትና ሶስት ቅጠል ብቻ እንዲኖራቸው ሆነው ይዘጋጃሉ።ለገበያ የሚቀርቡትም የአበባ ቁራጮቹ ብቻ እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የአበባ እርሻው ከአዲስ አበባ መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ቆቃ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን፤ 2500 ለሚደርሱ ሠራተኞች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል።የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው መካከልም አምስት በመቶ የሚያህሉት ባለሙያና በተመሳሳይ ሙያ ተመርቀው በዘርፉ ውስጥ ያሉ ናቸው።

ድርጅቱ ወደ ሥራው ከገባ 19 ዓመታትን ያስቆጠረና በዘርፉ ልምድ ማካበት የቻለ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተለያየ ጊዜ በሚዘጋጁ መሰል ኤግዚቢሽኖችም ተሳታፊ በመሆን ምርቱን የማስተዋወቅና የገበያ ትስስር መፍጠር የቻለም መሆኑን ይገልጻሉ።ትልቁ ገበያቸው በኢንተርኔት እንደሆነም ይጠቅሳሉ፡፡

በሬድፎክስ ኢትዮጵያ የሚመረቱት አበቦች ሮዝ ከሚባለው የአበባ ዝርያ እንደሚለዩ በመጥቀስም፤ አበባውን ከማልማታቸው አስቀድመው የደንበኞችን ፍላጎት እንደሚቀበሉም አቶ ሞሲሳ ተናግረዋል፤ አሁን ባለው ሁኔታ ጥሩ ገበያ መኖሩንም ይገልጻሉ።ዋናው መስሪያ ቤት ኔዘርላንድ ላይ ያለው በመሆኑ ገበያውን እዛ ያለው የማርኬቲንግ ባለሙያ ይቆጣጠረዋል ያሉት አቶ ሞሲሳ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ደግሞ አምርቶ መላክ ብቻ እንደሚጠበቅበትና የገበያ ችግር እንደሌለም ይናገራሉ።

በዓለም አቀፍ ገበያ በስፋት የሚታወቀው ሬድፎክስ ኢትዮጵያ አበባ አምራች አሜሪካና ካናዳ በየዓመቱ ሰፊ ገበያ ያለው ነው።በተጨማሪም አውሮፓ ላይ ብዙ ቦታዎች ላይ የአበባ ምርቶቹን ይሸጣሉ።በኤክስፖርት ላይ ያተኮረው የሆርቲካልቸር ዘርፍ ሻጭና ገዢም ቢሆን በውጭው ዓለም እንደሆነ ይታወቃል።

ዘርፉ ትልቅ ገበያን የሚፈልግ እንደመሆኑ ዕድሜ ጠገብ ገበያ ያለው ስለመሆኑ በኤግዚቢሽኑ ያገኘናት ወይዘሪት ሳባ ሰይድ አጫውታናለች።መቶ ዓመት ባስቆጠረው ሮያል ፍሎራ ሆላንድ ገበያ አካውንት ማናጀር በመሆን የምታገለግለው ሳባ፤ ሮያል ፍሎራ ሆላንድ በሆርቲካልቸር ዘርፍ ዓለም አቀፍ የሆነ ትልቁ ገበያ እንደሆነ ትናገራለች።

እሷ እንዳለችው፤ ዓለም አቀፉ ሮያል ፍሎራ ሆላንድ ኩባንያ አምራችና ገዢዎችን የሚያገናኝ እንደ ህብረት ሥራ አይነት ነው።ትልቅ የገበያ ቦታ ነው።ይህ ገበያም ዓለም አቀፍ ገዢዎችና ዓለም አቀፍ ሻጮችን የሚያገናኝ የገበያ ቦታ ነው።ዕድሜ ጠገቡ የገበያ ቦታ በአፍሪካ ዋናው ቢሮ ያለው ሲሆን፣ በኢትዮጵያም ቢሮ አለው።በአሁኑ ወቅትም ገዢና ሻጭ በቀላሉና በፍጥነት መገናኘትና መገበያየት የሚችሉበትን መንገድ በማመቻቸት እየሠራ ነው።

በዓለም ላይ ያሉ አበባ አምራቾችን እና አበባ ገዢዎችን በማገናኘት የሚሠራው ሮያል ፍሎራ ሆላንድ፣ በዘረጋው የገበያ ስርዓት በየትኛውም ዓለም ያለ ማንኛውም አበባ ገዢ በዲጂታል ሲስተም ባለበት ሆኖ አበባውን መግዛት ይችላል።ለተመረተው ለእያንዳንዱ አበባ እንደ አይነቱ የዋጋ ተመን ይቆረጥለታል።የገበያ ሂደቱም በቀጥታ መግዛትን ጨምሮ በጨረታ የሚሸጥ ይሆናል።በዚህም አምራቹም ሆነ ገዢው ባለበት ሆኖ መገበያየት ይችላል።

ሮያል ፍሎራ ሆላንድ ዓለም አቀፍ ገበያ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ አበባ አምራቾች 70 በመቶ ከሚሆኑት ጋር በጋራ እየሠራ እንደሆነ የጠቀሰችው ሳባ፤ በሆርቲካልቸር ዘርፍ ኢትዮጵያ ትልቅ አቅም እንዳላትም ትናገራለች። ዓለም አቀፍ የገበያ ቦታ የሆነው ሮያል ፍሎራ ሆላንድ ወደ ኢትዮጵያ ገበያ መቀላቀሉም በዚሁ ምክንያት ነው ትላለች።በሆርቲካልቸር ማለትም አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ በማምረት ኬንያ ከዓለም ቀዳሚ መሆኗን ጠቅሳ፣ ኢትዮጵያ ሁለተኛ ፣ ኢኳዶር ደግሞ ሶስተኛ እንደሆነች ነው የገለጸችው፡፡

ኢትዮጵያ ጥራት ያለውና የተለያዩ የአበባ ዝርያዎችን አምርታ ለዓለም ገበያ በማቅረብ ከዓለም ሁለተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ መሆኗን ጠቅሳ፣ አገሪቱ ከዚህ በበለጠ ዕምቅና ጥልቅ የሆነ አቅም እንዳላት ነው ሳባ የጠቀሰችው።ኬንያውያን ቀድመው ወደ ዘርፉ በመግባታቸው የቀዳሚነቱን ቦታ እንደያዙ ነው ያስረዳችው።

ኢትዮጵያ ለሆርቲካልቸር ዘርፍ ምቹ የሆነ የአየር ጸባይ እንዳላት በመጥቀስም፣ ከዚህ በበለጠ መሥራት የሚጠበቅባት እንደሆነ ገልጻለች።ከማምረት ባለፈ እንዲህ ባሉ ኤክስፖዎች ምርቶችን ማስተዋወቅና የገበያ ትስስር በመፍጠር ዓለም አቀፍ ገበያውን ይበልጥ በማስፋት አገሪቷ ከዘርፉ መጠቀም የሚገባትን እንድትጠቀም ማድረግ ይገባል ብላለች።

የሆርቲካልቸር አምራች ላኪዎች ማህበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ በበኩላቸው፤ ለስምንተኛ ጊዜ የተዘጋጀው የሆርቲካልቸር ዓለም አቀፍ ኤክስፖ ሁለት ዓላማዎችን ይዞ መዘጋጀቱን ይናገራሉ።የመጀመሪያው በሆርቲካልቸር ዘርፍ ያለውን የኢትዮጵያን ኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሁለተኛው ዓለም አቀፍ ገዢዎችና አምራቾችን እንዲሁም በዘር የተለያየ አበርክቶ ያላቸውን አካላት ማገናኘት ነው ይላሉ።ይህም እጅግ ስኬታማ ሆኖ መጠናቀቅ እንደቻለ ነው ያስረዱት፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ ከ30 በላይ አገራት ወደ አገር ውስጥ መጥተው የኤክስፖው ተሳታፊ መሆን ችለዋል።አምራችና ገዢውን ጨምሮ ግብዓት አቅራቢዎች፣ የሎጅስቲክስ አቅራቢ ኩባንያዎችና የተለያየ አገልግሎት አቅራቢዎች በኤክስፖው መገናኘት መቻላቸውን ጠቅሰው፣ በዚህም እጅግ ውጤታማ የሆነ ስምምነት ማድረጋቸውንና ይህም ለዘርፉ ዕድገት የሚኖረው አበርክቶ የጎላ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ማህበሩ ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ዘርፍ ያላትን ዕምቅ አቅም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲያስተዋውቅ እንደቆየ የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይም ይህንኑ አጠናክረው እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።አያይዘውም ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ማለትም አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ እምቅ አቅም እንዳላት አስታውቀው፣ ይህን እምቅ አቅም ደግሞ ትርጉም ወዳለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ መቀየር ያስፈልጋል ብለዋል።ለዚህም ኢንቨስትመንቱ እንደሚያስፈልግ፣ በዘርፉ የሚታዩ ማነቆዎች መፈታት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

አቶ ቴዎድሮስ ከዚህ ቀደም እንዲህ ያለ ኤክስፖ በየሁለት ዓመቱ ይካሄድ እንደነበር ያስታወሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኤክስፖው ውጤታማ በመሆኑ በቀጣይ በየዓመቱ ለማድረግ ማህበሩ ዝግጅት እያደረገ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።በአበባ ምርት ብቻ ሳይሆን በአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በዕጸጣዕም ምርትም እንዲሁ ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራ እንደሰራ አስታውቀዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የሆርቲካልቸር ዘርፍ ከአበባ በተጨማሪ አትክልትና ፍራፍሬን እንዲሁም ዕጸጣዕምን የሚጨምር ቢሆንም በስፋት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እየቀረበ ያለው የአበባ ምርት ነው።ይሁንና ካለፉት ዓመታት ይልቅ በዘንድሮ ዓመት የተሻለ የአትክልት፣ ፍራፍሬና ዕጸጣዕም ምርት ተገኝቷል።በቀጣይም ይህንኑ አጠናክሮ በማስቀጠል ዕጸጣዕምን ጨምሮ በአትክልትና ፍራፍሬ ብቻ ትልቅ ኤክስፖ ይዘጋጃል።

የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ወደ ዘርፉ ቢመጡ ራሳቸውን ጠቅመው አገራቸውን ይጠቅማሉ፤ የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ፣ የውጭ ምንዛሬን ማምጣት ይችላሉ።የተለያዩ የፖሊሲዎች አሉ።በተለይም ለዘርፉ የተሰጡ የኢንቨስትምት ማበረታቻዎች አሉ።እነዚህም በልማት ባንክና በሌሎች ባንኮች በኩል እየተቀረጹ ነው።ይህም የተሻለ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል፤ ስለዚህ ኢትዮጵያውያን በዘርፉ በስፋት ቢሰማሩ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ በማለት ሀሳባቸውን ቋጭተዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ስምን ይሆን መመሪያ የማናነበው?

**ዋለልኝ አየለ**

‹‹ማንበብ ልማዳችን አይደለም›› ሲባል ለመጽሐፍ፣ ጋዜጣና መጽሔት ብቻ ይመስላል፡፡ በአንድ ዓረፍተ ነገር ወይም ሐረግ ወይም በአንዲት ቃል ብቻ የተጻፉ ጽሑፎችንም አናነብም፡፡ አንድን ነገር ምን እንደሆነ የሚገልጽ ጽሑፍ ተጽፎ ልብ አንለውም፤ ይልቁንም በግምትና በዘፈቀደ ለማድረግ እንሞክራለን፡፡

ይህን ነገር ያስታወሰኝ ባለፈው እሁድ ከአንድ መምህር ጓደኛዬ ጋር በነበረን ጨዋታ ነው፡፡ አንድ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ ገዝተን ወደ ቤት ገባን፡፡ ዋጋውን ከባለፈው ዓመት ጋር እያነፃፀርን ስንገረም ቆይተን ‹‹በዚህ ዋጋ ተገዝቶ ለረጅም ጊዜ ቢያገለግልስ ጥሩ አልነበር!›› በሚል ቶሎ ስለመበላሸቱም ሀሳብ ተነሳ፡፡ ለመበላሸቱ ግን የምርቶች ጥራት እንዳለ ሆኖ የአጠቃቀም ስህተቶችም አሉ፡፡ ይህን ስናስታውስ ከዕቃው ጋር የተሰጠች ዝርዝር መመሪያ የያዘች ወረቀት ማንበብ ጀመርኩ፡፡ በዚያው እግረ መንገድ መመሪያ ባለማንበብ ብዙ ነገር እንደምናበላሽ ስናወራ ቆየን፡፡

በልጅነቴ አንድ ጥሩ ልማድ ነበረኝ፡፡ የፋብሪካ ዕቃዎች የታሸጉበት ሸፋን ላይ ወይም ራሱ ዕቃው ላይ ጽሑፍ አላቸው፡፡ ጽሑፎቹ አብዛኛውን ጊዜ እንግሊዘኛ ናቸው። የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ የፋብሪካ ዕቃዎች ላይ ያሉ ጽሑፎችን እያዟዟርኩ ነበር የማነብ፡፡ ችግሩ ግን እኔ የማነበው ስለዕቃው አጠቃቀም ለማወቅ ሳይሆን እንግሊዝኛ ማንበቡ ብርቅ ስለሚሆንብኝ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹን ትርጉማቸውንም አላውቀውም፡፡ ቢሆንም ግን እያዟዟርኩ አነብ ነበር፡፡ የትምህርት ደረጃዬ ከፍ እያለ ሲሄድ ግን በተቃራኒው ሰነፍ እየሆንኩ ሄድኩ፤ ከዕቃዎች ላይ ያሉ ጽሑፎችን ማንበብ ትዝ አይለኝም፡፡

አሁን ላይ ሳስበው የእኔ ችግር ብቻ አይደለም፤ አንደ ቁም ነገር የሚቆጥረው የለም፡፡ በተለይም ትልልቅና በውድ ዋጋ የሚገዙ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን ስንገዛ ወረቀቱን ከታሸገበት ካርቶን ጋር ነው የምንጥለው፡፡ እንኳን ወረቀቱን ከራሱ ከዕቃው ላይ ያለውን ጽሑፍ እንኳን አናነበውም፡፡ አውቀነው ቢሆን እኮ ችግር አልነበረውም! አብዛኞቻችን ግን ሳናውቀው ነው የማናነበው፡፡

አብሮን ያልኖረ የፋብሪካ ዕቃ ስንጠቀም መመሪያውን ከማንበብ ይልቅ ሰዎችን በመጠየቅ ወይም በልማድ በማየት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መመሪያው ከላዩ ላይ እያለ በዘፈቀደ ለመገጣጠም ወይም ለማሰራት እንታገላለን። እንዴት መሰካካት እንዳለበት ጠቋሚ ምልክቶች እያሉ በግድ ለመሰካት እንታገላለን፤ እምቢ ካለ እያዟዟርን መታገል ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ዕቃው ለብልሽት ይዳረጋል፡፡ በተለይም የምልክት ጠቋሚዎችን ልብ አንልም፡፡

መመሪያ አለማንበብ ዕቃ ማበላሸትን ያስከትላል ማለት ነው፡፡ የገዛነውን ዕቃ ያለአግባብ አበላሸን ማለት ለኪሳራ ተዳረግን ማለት ነው፡፡ ይሄ ማለት ማንበብ አለመውደዳችን በሕይወታችን ላይ ጉዳት እያመጣ ነው ማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ ግን አንድ ልብ መባል ያለበት ነገር አለ። ብዙ የፋብሪካ ምርቶች መመሪያዎቻቸው የሚጻፈው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ አብዛኞቹ የሚመረቱት ውጭ አገር ስለሚሆን ነው፡፡ ዳሩ ግን የአገር ውስጥ ምርቶችም ቢሆን ዓለም አቀፍ ለማድረግ ሲባል መመሪያቸው የሚጻፈው በእንግሊዝኛ ነው፡፡ እንግሊዝኛ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በትምህርት የሚገኝ እንጂ በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎቻችን ውስጥ ያለ አይደለም። የማህበረሰቡ ቋንቋ አይደለም፤ በሃይማኖት ተቋማት እና በጎልማሶች ትምህርት የሚማሩ ሰዎች እንግሊዝኛ አንብበው ላይረዱ ይችላሉ፡፡

ይህ ግን ለስንፍናችን ምክንያት አይሆንም፤ ምክንያቱም አፋችንን በፈታንበት ቋንቋ የተጻፉ መመሪያዎችንም አናነብም፡፡ በአማርኛ አፉን የፈታ ሰው የአማርኛ መመሪያዎችን አያነብም፡፡ የእንግሊዝኛ ዜናዎችን፣ የእንግሊዝኛ ልቦለዶችን የሚያነቡ ሰዎች መመሪያዎችን ግን አያነቡም፡፡ ስለዚህ የቋንቋ ገደብ ብቻ ሳይሆን ልብ አለማለት(ስንፍና) ነው፡፡

መመሪያዎችን አለማንበብ ለወንጀል ሁሉ ይዳርገናል። ‹‹ሕግን አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም›› የሚባል ተደጋጋሚ መሪ ቃል አለ፡፡ መመሪያዎችን አለማንበብም ከተጠያቂነት አያድንም፡፡ ብዙ ጊዜ መደረግ የሌለባቸው ነገሮች በጽሑፍ ተከልክለው ሳለ ባለማንበብ ብቻ እናደርጋቸዋለን፡፡ ‹‹ማለፍ ክልክል ነው›› የሚል ተጽፎ ባለማንበብ ብቻ ከፖሊስ ጋር ግብ ግብ እንገጥማለን፡፡ ፎቶ ማንሳት ክልክል መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ያለበት ቦታ ላይ ፎቶ አንስተን ልንጠየቅ እንችላለን፡፡ በአጠቃላይ ከፍተኛ የፀጥታ ገደብ ያለባቸው አካባቢዎች ላይ መመሪያ ባናነብ ለወንጀል ልንዳረግ እንችላለን፡፡

መመሪያ ማንበብ መለማመድ ያለብን ከታች ከትምህርት ቤት ጀምሮ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የፈተና ትዕዛዞች ጥሩ መለማመጃ ናቸው፡፡ አስታውሳለሁ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ እያለሁ አንዳንድ መምህራን ከጥያቄው ይልቅ በመመሪያ(ትዕዛዝ) ይሸውዱን ነበር፡፡ ጥያቄው ሳይከብደን በመመሪያ ስህተት አንድ ትዕዛዝ የሚይዛቸውን ሙሉ ነጥቦች እናጣለን፡፡ የሚገርመው በመመሪያ ስህተት የሚሸወዱት ጎበዝ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ሮጠው ወደ ጥያቄው ስለሚሄዱ በተለመዱት ትዕዛዞች ብቻ ነው መልሱን የሚሞሉት፡፡

ለምሳሌ፤ ትዕዛዙ ‹‹ትክክል የሆነውን ሀሰት፣ ትክክል ያልሆነውን ደግሞ እውነት በማለት መልሱ›› የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜ የተለመደው ትክክል የሆነውን እውነት፣ ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ሀሰት ማለት ስለሆነ የጥያቄዎች ይዘት ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ ትዕዛዝ ያው ትዕዛዝ ነውና ነጥብ እናጣለን፡፡

አሁን ያለው መመሪያ ያለማንበብ ችግራችን ግን ልብ አለማለት ብቻ አይደለም፤ ጭራሹንም አለማየት ሆነ እንጂ። እንዲህ አይነት ጥቃቅን ስህተቶች እየተለመዱ ሲሄዱ ትልቅ አደጋ ላይ የሚጥሉ መመሪያዎችን አለማስተዋል ይከሰታል። የተሰጠንን ትልቅ አገራዊ ኃላፊነት ያለመመሪያ መሥራት ይመጣል፡፡

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ የዕቃዎች መመሪያ ለሌሎች ነገሮችም ልምድ ይሆነናል፡፡ የምንጠጣውን የታሸገ ውሃ እንኳን የማዕድን ይዘቶችን ስንቶቻችን እናነባለን? እዚህ ላይ አንድ ገጠመኝ ልጨምር፡፡

ከምኖርበት ቤት አጠገብ ካለ አንድ ሱቅ ውሃ እየገዛሁ ነው፡፡ የሶዲየም ይዘቱ መብዛት የለበትም ሲባል ስለምሰማ ሶዲየም እያየሁ ነው የምገዛ፡፡ እንደተለመደው የሶዲየም ይዘቱን ሳይ ‹‹ምንነቱን ነው የምታየው?›› አለችኝ፡፡ የሶዲየም ይዘቱን መሆኑን ስነግራት ተገረመች፤ ማንም እንደዚያ አይቶ እንደማያውቅ ነገረችኝ፡፡ የውሃውን ስም እንኳን ‹‹ይሄኛው ይሁንልኝ›› የሚሉት አብዛኞቹ በፕላስቲኩ ጥንካሬ እንጂ በውሃው ይዘት አይደለም፡፡ ይቺን እንኳን ትንሿን ነገር ልብ አንልም፡፡

እዚህ ላይ የአንድ ጋዜጠኛ ጓደኛዬን ተሞክሮ ብገልጽ ጥሩ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይህ ጋዜጠኛ የተጻፈ ነገር አያልፈውም።ካፌ ውስጥ ለተጠቀምነው ነገር ደረሰኝ ሲመጣ ከዋጋው ውጭ ያሉ ቃላትና ቁጥሮችን ሁሉ ያነባቸዋል፡፡ ብዙዎቻችን የምናነበው ድምር ዋጋውን ብቻ ነው፤ ግፋ ቢል ደግሞ ያልተጠቀምነውን ነገር እንዳይጨምሩ(ሆን ብለውም ሆነ ተሳስተው) የተጠቀምነውን ዝርዝር ነው የምናነበው፡፡ እሱ ግን ከላይ ከአናቱ ጀምሮ የንግድ ስሙን ሁሉ ነው፡፡

ለምንድነው ይህን ሁሉ የምታነበው ስንለው ‹‹የሙያ ቃላት አገላለጽ›› የሚለው አለው፡፡ ይሄ ማለት በየዘርፉ ያሉ የሙያ ቃላትን ማወቅ ይፈልጋል ማለት ነው፡፡ የንግድ፣ የህክምና፣ የወታደራዊ... በአጠቃላይ በምን ዘርፍ ምን አይነት አገላለጽ እንዳለ እየተማረ ነው የሚሄድ፡፡

አንዳንዱ ለመማሪያ ጭምር እዚህ ድረስ በትኩረት አድርጎ ሲያነብ አንዳንዶቻችን ግን የግዴታ የሆነውን እንኳን አናነብም! ይህን ልማዳችንን እንቅረፍ፤ መመሪያዎችን እናንብብ!

# ዓለም አቀፍ

## ናሳ ወደ ጨረቃ የሚልካቸውን የመጀመሪያዎቹን ሴት እና ጥቁር ይፋ አደረገ

የአሜሪካው የጠፈር ድርጅት ናሳ ከ50 ዓመታት በኋላ የሰው ልጅን ወደ ጨረቃ ለመውሰድ በያዘው ዕቅድ መሠረት አራት ጠፈርተኞች ማዘጋጀቱን ይፋ አድርጓል። ክርስቲና ኮች ለጨረቃ ተልዕኮ የተመደበች የመጀመሪያዋ ሴት ጠፈርተኛ ትሆናለች። ቪክተር ግሎቨር ደግሞ የመጀመሪያው ጥቁር ጠፈርተኛ ይሆናል ተብሏል።

ሁለቱ ጠፈርተኞችን ጨምሮ ሪድ ዊስማን እና ዠርሚ ሃንሰን በሚቀጥለው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ ወይም በ2025 መጀመሪያ ላይ ወደ ጨረቃ ያቀናሉ። ጠፈርተኞቹ በጨረቃ ላይ ባያርፉም ተልዕኳቸው በቀጣይ ጠፈርተኞች ለሚያደርጉት ጉዞ መንገድ ይከፍታል ተብሏል። ሦስቱ የአሜሪካ ዜጎች እና ብቸኛው ካናዳዊ በሂዩስተን ቴክሳስ በተካሄደ ስነ ስርዓት ለሕዝብ ይፋ ተደርገዋል።

ጠፈርተኞቹ ለጉዞው ራሳቸውን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ስልጠና ይጀምራሉ ተብሏል። ሴት እና ጥቁር ጠፈርተኛ በመምረጥ ናሳ ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ጠፈርተኞችን ለመምረጥ የገባው ቃል እንደጠበቀ ተገልጿል። ሁሉም ከዚህ ቀደም ወደ ጨረቃ የተደረጉ ተልዕኮዎች በሙሉ በነጭ ሰዎች የተከናወኑ ናቸው።

የሪድ ዊስማን የዩናይትድ ስቴትስ የባህር ኃይል አብራሪ ሲሆን ለተወሰነ ጊዜ የናሳ የጠፈር ምርምር ቢሮ ኃላፊ ሆኖ አገልግሏል። እአአ በ2015 በቀድሞ የጠፈር ተልዕኮ ወደ ዓለም አቀፍ የጠፈር ጣቢያ ተጉዟል። ቪክተር ግሎቨር ናሳን የተቀላቀለው እአአ በ2013 ሲሆን የመጀመሪያ የጠፈር ተልዕኮውን በ2020 አከናውኗል። ለስድስት ወራት በህዋ ጣቢያ መቆየት የቻለ የመጀመሪያው ጥቁር ሆኗል።

ክርስቲና ኮች በሙያዋ የኤሌክትሪክ መሐንዲስ ናት። ለ328 ቀናት በመቆየት የሴቶችን ክብረ ወሰን ሰብራለች። ከናሳ ጠፈርተኛዋ ጄሲካ ሜየር ጋር በ2019 በሴቶች ብቻ በተደረገ የጠፈር ጉዞ ላይ ተሳትፋለች። ዠርሚ ሃንሰን የካናዳ የጠፈር ኤጀንሲን ከመቀላቀሉ በፊት በሮያል ካናዳ አየር ኃይል የተዋጊ ጄት አብራሪ ነበር። ወደ ጠፈር እስካሁን አልተላከም።



“የአርተሚስ-2 ጠፈርተኞች እኛን ወደ ጨረቃ ለመውሰድ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የሚደክሙ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ይወክላሉ” ሲሉ የናሳ አስተዳዳሪ ቢል ኔልሰን ተናግረዋል። “የናሳ ጠፈርተኞች ሪድ ዊስማን፣ ቪክተር ግሎቨር እና ክሪስቲና ሃሞክ ኮች እና የሲኤስኤ ጠፈር ተመራማሪው ዠርሚ ሃንሰን የራሳቸው ታሪክ አሏቸው። በአንድነት ግን መግለጫችንን ይወክላሉ። ለአዲሱ ትውልድ ኮከብ ጠፈርተኞች እና ህልም ላላቸው አዲስ የምርምር ዘመን እየፈጠርን ነው” ብለዋል።

ወስማን የጉዞው አዛዥ ይሆናል። ግሎቨር የእሱ አብራሪ ሲሆን ኮች እና ሃንሰን ደግሞ ለ“ተልዕኮው” ድጋፍ ሰጪዎች ይሆናሉ። አራቱ በ1968 በአፖሎ 8 የተካሄደውን ተልዕኮ ይደግማሉ። ይህም የሰው ልጅ ወደ ጨረቃ የደረሰበት መጀመሪያው የጠፈር በረራ ነበር።

ሰራተኞቹ ቤታችን ፕላኔታችን ከጨረቃ አድማስ ጀርባ መውጣቷን የሚያሳየውን ታዋቂውን “Earthrise” ምስል አነሱ። ዋነኛው ልዩነት ናሳ በአርተሚስ ፕሮግራሙ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ቴክኖሎጂ መጠቀሙ ነው። በግሪክ አፈ ታሪክ መሠረት አርተሚስ የአፖሎ መንታ እህት ነበረች። ባለፈው የፈረንጆች ዓመት ድርጅቱ አዲሱን የጨረቃ ሮኬቱን የስፔስ ላውንች ሲስተም እና ተያያዥነት ያላቸውን የሰራተኞች ማጓጓዣ ኦሪዮንን ሞክሯል።


በዚህ የአርተሚስ-1 ተልዕኮ ምድርን በመልቀቅ ያለምንም ጠፈርተኛ በጨረቃ ዙሪያ ለ25 ቀናት ጉብኝት አድርጓል። በዚህም መሐንዲሶች የመሣሪያውን ዝግጁነት እንዲገመግሙ አስችሏቸዋል። ይፋ የተደረጉት ጠፈርተኞች ኦሪዮንን በመጠቀም በአርተሚስ-2 ወደ ጨረቃ የደርሶ መልስ ጉዞ ያደርጋሉ። ይህም 10 ቀናትን ያህል ሊወስድ ይችላል።

ለመጨረሻ ጊዜ የሰው ልጅ ወደ ጠፈር በረራ ያደረገው በ1972 በአፖሎ 17 ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ጠፈር ላይ ያረፈው ደግሞ በአፖሎ 11 በ1969 ነበር። አርተሚስ-3 ወደ ጅራ ለመግባት ቢያንስ ከአርተሚስ-2 በኋላ እስከ 12 ወራት ድረስ ይወስድበታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ናሳ ጠፈርተኞችን ወደ ጨረቃ እንዲራመዱ የሚያስችል ስርዓት እስካሁን የለውም። ይህ በቢሊየነሩ ኢሎን መስክ ስፔስ ኤክስ ኩባንያ እየተዘጋጀ ይገኛል። ስታርሺፕ ተብሎ የሚጠራው ተሽከርካሪው በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት የበረራ ሙከራ ይጀምራል።

“በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አጋጣሚ ማክበር አለብን፤ ምክንያቱም አርተሚስ-2 ከጨረቃ ደርሶ መልስ ተልዕኮም በላይ ነው። ሰዎችን ወደ ጨረቃ ወለል ከመላካችን በፊት መከናወን ያለበት ተልዕኮ ነው። ወደ ማርስ ለሚደረገው ጉዞ ቀጣዩ ደረጃ ነው ሲል ቪክተር ግሎቨር በሂዩስተን ሥነ ሥርዓት ወቅት ተናግሯል።

ክርስቲና ኮች በበኩሏ”ደስተኛ ናችሁ? ይህንን ጠየቅሁት ደስታዎን፣ ምኞቶችዎንና ህልሞችዎን ከእኛ ጋር በዚህ ተልዕኮ ይዘን ስልምጓዝ ነው” ብላለች። ቫኔሳ ዋይሽ የተልዕኮው የቁጥጥር ጣቢያ በሆነው የናሳ ጆንሰን የጠፈር የበረራ ማዕከል ዳይሬክተር ናት። “[ከአርተሚስ-2] ጠፈርተኞች መካከል የመጀመሪያዋ ሴት፣ የመጀመሪያው ጥቁር እና የመጀመሪያው ካናዳዊ በጨረቃ ተልዕኮ ላይ ይገኛሉ። አራቱም የጠፈር ተመራማሪዎች የሁሉንም ጥቅም ለማግኘት በመሞከር የሰው ልጅ ይወክላሉ” ማለቷን ቢቢሲ ዘግቧል።




# ስፖርት

## አሰልጣኝ ውበቱ ለዋልያዎቹ ደካማ አቋም ሊጉን ወቀሱ

**ብርሃን ፈይሳ**

ለ2023 የኮትዲቯር አፍሪካ ዋንጫ ሶስተኛና አራተኛ የምድብ ማጣሪያ ጨዋታዎቹን ከጊኒ አቻው ጋር ሞሮኮ ላይ ያደረገው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) አንድም ነጥብ ማግኘት ሳይችል ወደ አገሩ ተመልሷል። በዚህም ወደ አፍሪካ ዋንጫው የማለፍ እድሉ የጠበበ ሆኗል። የዋልያዎቹ አለቃ አሰልጣኝ ውበቱ አባተ ከሁለቱ የጊኒ ጨዋታ ሽንፈቶች በኋላ እዚያው ሞሮኮ እያሉ መግለጫ መስጠታቸው የሚታወስ ሲሆን ወደ አገር ቤት ተመልሰው የሚሰጡት መግለጫም ተጠባቂ ነበር።

አሰልጣኝ ውበቱ ከፌዴሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ባህሩ ጥላሁን ጋር በመሆን ከትናንት በስቲያ በፌዴሬሽኑ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከጊኒ አቻቸው ጋር በነበራቸው የ180 ደቂቃ ጨዋታ ዙሪያ በሰጡት መግለጫም ዋልያዎቹ ላሳዩት ደካማ አቋም ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አንዱ ምክንያት መሆኑን በመግለፅ ወቀሳቸውን አቅርበዋል።

በሊጉ የሚታየው እንቅስቃሴ ቡድኑ ውስጥ ስላሳረፈው ጫና የተጠየቁት አሰልጣኝ ውበቱ "ሊጉም ይቋረጣል ወጥ የሆነ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ክለቦች ማነስ አይተናል፣ የተጨዋቾች ወጥ አቋም ማየት ላይ አስቸጋሪ ሆኖብናል፣ ሌሎች ሀገሮች ወጥ ብሔራዊ ቡድን አባላት ይኖራቸውና አንድ ሁለት ሊቀይሩ ይችላሉ እኛ ግን ሁለት አመት የሚቆዩ ወጥ ተጨዋቾች ማግኘት ተቸግረናል፣ በአጭር ቀናት ውስጥ መጫወት ጫና አለው ሜዳ በተመለከተ አሁንም ችግር ነው በመጥፎ ሜዳ ላይ የሚጫወቱ ወደ ጥሩ ሜዳ ሲመጡ ክፍተት ይፈጠራል፣ ይሄም አንድ ችግር ነው" በማለት የተናገሩ ሲሆን ከጊኒ ጋር በነበረው ጨዋታ ግን ከሜዳውና ከሊጉ ይልቅ ተጠያቂ የሚያደርጉት የራሳቸውን ቡድን ዝግጅት መሆኑን አስረድተዋል።



**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝ ውበቱ አባተ፣**

ዋሊያዎቹ ወደ ኮትዲቯር የአፍሪካ ዋንጫ የማለፍ ዕድላቸው መጥበቡን የገለፁት አሰልጣኝ ውበቱ፣ " ከጊኒ ጋር ማሳካት የፈለግነውን ውጤት አላሳካንም፣ የመጀመሪያው ጨዋታ ደካማ አቋም አሳይተናል፣ ሁለተኛው በንጽጽር የተሻለ ነበር፣ ያም ሆኖ በተገኘው ውጤት መሰረት ወደ ኮትዲቯር የአፍሪካ ዋንጫ የማለፍ ዕድላችን ጠቧል" ሲሉ ተናግረዋል።

አሰልጣኙ እንደሚሉት "ከመጀመሪያው የኒጀር ጨዋታ ጀምሮ ቡድኑ ጥሩ መደላደል ላይ ነበር ማለት አይቻልም፣ በሁለቱ አመታት ውስጥ በአፍሪካ ዋንጫ ላይ መገኘት በራሱ ስኬት ነው፣ እኛ እንደ አልጄሪያ ግብጽና ናይጄሪያ በየአፍሪካ ዋንጫው የምንገኝ አይደለንም እናም በሻምፒዮናው ላይ መገኘታችንን እንደ ስኬት እቆጥራለሁ፣ ውድድሩ ላይ ገብተን ያሳየነው ድክመት ግን መሻሻል አለበት። ስኬታማ ነኝ ብለው ያስባሉ ወይ? ተብ ለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡም፣ "ወደ ኮትዲቯር የአፍሪካ ዋንጫ የማለፍ ዕድላችን ጠቧል በቀጣይ ግብጽን ስንገጥም የምንችለውን እናደርጋለን ለወደ ፊትም ሽንፈት ቢገጥመን ዋናው ጉዳይ ከሽንፈት መነሳት ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

ቡድኑ እየተመራ ይስቁ ስለነበሩ ተጨዋቾች የተጠየቁት አሰልጣኙ "እንኳን ተጨዋቾቼ ማንም በቡድኑ ሽንፈት አይስቅም ለምን ሳቁ የሚለው ግን መታየትና መመርመር አለበት" ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

አሰልጣኝ ውበቱ ከወራት በፊት ዋልያዎቹን በማሰልጠን እንዲቀጥሉ ተጨማሪ የሁለት አመት ኮንትራት ሲሰጣቸው ቡድኑን ለአፍሪካ ዋንጫ የማብቃት ኃላፊነት አብሮ እንደተሰጣቸው ይታወሳል። ይህ ካልሆነም አሰልጣኙ ከቡድኑ ጋር እንደሚለያዩ በርካቶች ጠብቀዋል። ዋልያዎቹ ወደ አፍሪካ ዋንጫ የሚያልፉበት እድል ከጊኒው የደርሶ መልስ ጨዋታ በኋላ መጥበቡን ተከትሎ አሰልጣኝ ውበቱ ከቡድኑ ጋር ስለሚኖራቸው ስንብት አስበው ያውቃሉ ተብለው በመግለጫው የተጠየቁት ሲሆን "ቀሪ ኮንትራት አለኝ በድንገት ተነስቼ የምወስነው ነገር የለም፣ ከቀጣሪዎቼ ጋር መነጋገር ይኖርብኛል፣ ምንም የሚያስቸኩል ነገር የለም" ሲሉ መልሰዋል።

ከተጨዋቾቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄም፣ "የማስገባቸው ተጨዋቾች ደስ ሊላቸው የማይገቡት ደግሞ ቅር ሊላቸው ይችላል፣ ነገር ግን ሁሉም ለህግና ስርዓት ሊገዙ ይገባል፣ ከዚያ ውጭ በግሌ ከማንም ጋር ችግር የለብኝም " በማለት መልስ ሰጥተዋል።

ፌዴሬሽኑ ከአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ጋር ስላለው ውል ዝርዝር የተጠየቁት የፌዴሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ባህሩ ጥላሁን በበኩላቸው "ከአሰልጣኝ ውበቱ ጋር መነጋገራችን አይቀርም፣ ከአሰልጣኙ ጋር በነበረው ውል ዙሪያ የቱ ተሳካ ..? ምኑስ አልተሳካም የሚለውን የፌዴሬሽኑ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አይቶ በቀጣይ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፣ አሁን ላይ ግን ምንም መናገር አልችልም" ሲሉ ተናግረዋል።

በማጣሪያው በምድብ አራት ከግብጽ፣ ማላዊ እና ጊኒ ጋር የተደለደሉት ዋልያዎቹ ሁለት ጨዋታዎች ብቻ ይቀሩታል። ይህንን ተከትሎም አሰልጣኙ ከሽንፈት በኋላ እንዴት አገግሞ መመለስ ይቻላል የሚለው ላይ እንደሚያተኩሩ ጠቁመዋል።" የአንድ ቀን መውደቅ የሁልጊዜ መገለጫ ተደርጎ መታየት የለበትም" የሚሉት አሰልጣኝ ውበቱ፣ እስካሁን የነበረው ስነልቦና መሰናክል ቢያገኘውም ከዚያ ስሜት መውጣት የግድ መሆኑን አስረድተዋል። ምናልባትም ቡድኑ ከውድድሩ ወጥቶ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ከዚህ ቀደም እንደታዩ የከፉ ሽንፈቶች አይደሉም፡፡ በመሆኑም ቡድኑ በውድድር እስካለ ድረስ ለቀጣይ መታገል የግድ ነው፡፡ ቀጣይ ተጋጣሚዎቻችን በነጥብ የራቁን ቢሆንም አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ የግድ ነው፡፡


## ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

የጉምሩክ ኮሚሽን በዋናው መ/ቤትና በሥሩ በሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ባለው የሕግ ባለሙያ ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሥራ ፈላጊዎችን አወዳድሮ በቋሚነት ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

**ለክፍት የሥራ መደቦቹ የሚያመለክቱ ሥራ ፈላጊዎች፡-**

1. የተጠቃለለ የመመረቂያ ነጥባቸው ቢያንስ 2 እና ከዚያ በላይ ያላቸው
2. በሕግ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውና የመውጫ ፈተና ወስደው ያለፉ መሆን አለባቸው፡፡
3. በተቋሙ ከተቀጠሩ በኋላ ቢያንስ ለአምስት ዓመት ለማገልገል ፍቃደኛ የሆኑ፡፡
4. በሥራ ልምድ የሚወዳደሩ አመልካቾች ከሚሠሩበት መሥሪያ ቤት የሥነ-ምግባር መግለጫ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፡፡

**ስለሆነም ሥራ ፈላጊዎች ይህ ማስታወቂያ ከወጣ ከሦስት ተከታታይ ቀናት በኋላ ባሉ ስድስት ተከታታይ የሥራ ቀናት (ከሰኞ እስከ አርብ ) ውስጥ፡-**

* በየትኛውም ክፍት የሥራ መደብ ላይ መቀጠር የሚፈልጉ ሥራ ፈላጊዎች መሿለኪያ ጥላሁን አደባባይ ፊት ለፊት በሚገኘው ዋና መ/ቤት 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 8 ወይም በሚቀርባቸው የኮሚሽኑ ቅ/ጽ/ቤቶች መመዝገብ የሚችሉ መሆኑን እያሳሰብን፤ ቅ/ጽ/ቤቶቻችን በባሕርዳር፣ በአዋሽ፣ በሰመራ፣ በጋላፊ፣ በኮምቦልቻ፣ በጅግጅጋ፣ በድሬዳዋ፣ በሞያሌ፣ በጅማ፣ በሀዋሳ፤ በአዳማ እና በሞጆ ከተሞች የሚገኙ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

*ሥራ ፈላጊዎች ለምዝገባ ሲመጡ የትምህርት እና የሥራ ልምድ ማስረጃቸውን ዋናውንና የማይመለስ አንድ ፎቶ ኮፒ ይዘው መምጣት አለባቸው፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ብዛት | የተፈላጊ ችሎታ መስፈርት | | ደመወዝ | የሥራ መደቡ የሚገኝበት ቦታ እና የሚፈለገው የሰው ኃይል ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ትምህርት | ቀጥታ የሥራ ልምድ | | |
| 1 | ጀማሪ የሕግ ባለሙያ | 7 | 21 | በህግ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ | 0 ዓመት | 9,246.00 | ለዋናው መ/ቤት 5፣ ለአ.አ ቃሊቲ 2፣ ለሞጆ 3፣ ለአ/አ ኤርፖርት 1፣ ለኮምቦልቻ 1፣ ለድሬዳዋ 2፣ ለጋላፊ 1፣ ለአዋሽ 1፣ ለጅማ 1፡ ለጅግጅጋ 1 ፣ ለሠመራ 1፣ ለአዳማ 2 |
| 2 | የሕግ ባለሙያ | 8 | 8 | በህግ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ | 2 ዓመት | 13,184.00 | ለዋናው መ/ቤት 1፣ አ/አ ኤርፖርት 1፣ ባህርዳር 1፣ ኮምቦልቻ 1፣ ድሬዳዋ 1፣ አዋሽ 1፣ ጅማ 1፣ ጅግጅጋ 1 |
| 3 | ከፍተኛ የሕግ ባለሙያ I | 9 | 12 | በህግ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ | 4 ዓመት | 15,743.00 | ለዋናው መ/ቤት 6፣ አ.አ ቃሊቲ 1፣ አ/አ ኤርፖርት 1፣ ባህርዳር 1፣ ጋላፊ 1፣ ሠመራ 1፣ ጅግጅጋ 1 |
| 4 | የሕግ አገልግሎት ቡድን አስተባባሪ | 11 | 4 | በህግ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ | 6 ዓመት | 20,330.00 | ለኮምቦልቻ 1፤ጋላፊ 1፤ጅግጅጋ 1 ፣ ሠመራ 1 |

**ማሳሰቢያ፡-**

5. ሥራ ፈላጊዎች መቀጠር የሚፈልጉበትን አንድ ቦታ ብቻ በሥራ መጠየቂያ ቅፅ ላይ በግልፅ ማመልከት አለባቸው፡፡
6. የፈተና ቀን፣ ቦታና ሰዓት በአዲስ አበባ ዋናው መ/ቤት ለተመዘገቡ በዋናው መ/ቤት የውስጥ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የሚገለጽ ሲሆን ከአዲስ አበባ ውጭ በሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ለመቀጠር ለሚያመለክቱ ሥራ ፈላጊዎች በተመዘገቡበት ቅ/ጽ/ቤት የውስጥ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ይገለጽላቸዋል፡፡
7. ክፍት የሥራ መደቡ ፆታ አይለይም፡፡
8. ሴቶች ይበረታታሉ፡፡
9. ከምዝገባው ቀን ቀድመውም ሆነ ዘግይተው የሚመጡ ሥራ ፈላጊዎችን የማናስተናግድ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የጉምሩክ ኮሚሽን**